1. ሁሉም ለምን ያልፋል?

(በእውቀቱ ስዩም)

የጣፈንታ መዳፍ

ደስታና መከራን: እያፈሰ ሲናኝ

"ሁሉም ያልፋል " ብሎ : ማነው የሚያፅናናኝ?

ግራ በተጋባ :በዞረበት አገር

ካንቺ የምጋራው :ሰናይ ሰናይ ነገር

ፊቴን የሚያበራው :ያይንሽ ላይ ወጋገን

ዛሬ ተለኩሶ : የሚያሳየኝ ነገን

ለምን ሲባል ይለፍ : ያንን መሳይ ፍቅር

ደሰታሽ ይገተር: ሳቅሽ ቆሞ ይቅር!!

በብሩህ ቀላማት የተሸላለመ

-የተዋበ ህልሜ

በሁለት ጦርነት: መካከል የቆመ

-አጭሩ ሰላሜ

ያፍላነት ወኔየ : የጉርምስና አቅሜ

ነበር ተብሎ እንዳይቀር :እንዳገኘው ወትሮ

ባለበት ላይ ይቁም :ባስማት ተገትሮ::

እና

ከጣፈንታ መዳፍ: ሞልቶ ከሚፈሰው

በሰው የሚደርሰው

ለሰው የሚደርሰው

በጊዜ ኬላ ላይ : ተዛዝሎ ሲሰለፍ

በጎ በጎው ይቆይ : ክፉ ክፉ ይለፍ!!

2. የተከፈተ በር

(በውቀቱ ስዩም)

የቤታችን በሩ ፤

ከፍተሽው እንደሄድሽ ፤ዛሬም አልተዘጋም

የነበረኝ የለም፤ ለቀማኛ አልሰጋም

እምቢ ካልሽ እምቢ ነው ፤ፅኑ ነው ያንች ቃል

እንደማትመለሽ ፤አእምሮየ ያውቃል

ግን አልፈርድበትም፤ልቤ ቢያመነታ

ምኞት በሞላው ቤት ፤እውቀት የለው ቦታ

ተስፋ አይቆርጥም ደሞ፤

ልቤ ህልሙን ያምናል

ይለኛል ደጋግሞ፤

“ትመለስ ይሆናል

ትመለስ ይሆናል

ትመለስ ይሆናል፤”

እኔም በምላሹ ፤ ልቤን ፊት ሳልሰጠው

እንዲህ እለዋለሁ፤ ተስፋ ላስቆርጠው

“ጠጠር ላይቀቀል፤ አልማዝ ላይከለስ

በደመና ራስጌ፤ ጎጆ ላይቀለስ

እኔም አልሻሻል፤ እሱዋም አትመለስ፤

ሰማይ ሰም ይመስል፤ ቢንጠባጠብ ቀልጦ

የረር ፈልሶ ቢሸሽ፤ ቢከተል እንጦጦ

ባህሮች ቢከስሙ፤ ምድር ብትናወጥ

እሱዋም አትመለስ ፤እኔም አልለወጥ”

በዙርያየ ያለው ፀጋ ብዙ ነበር፤

ግና ክንፍ አብቅሎ

ፍቅርሽ ጥሎኝ ሲበር

ከኔ ጋር የቀረው

የተቆለፈ ልብ፤ የተከፈተ በር።

3. ' ንባበ-አዕምሮ ዘ እንቁራሪት '

('ዕሻራሀሐሴ 19/1970 ፈቃደ አዘዘ)

ወንዝ ነው ሀገሬ

ኩሬ ነው መንደሬ::

ብቻዬን ዘምሬ

ብቻዬን ዘፍኜ ;

የምል ዘንካታ ነኝ

"ድንቅ ነው ዘፈኔ የዜማው ቅላፄ

አይነሳ ድምፄ"

ድፍን እንቁራሪት; በየወንዝ መንደሩ ሲያንቋራ ... .ሲዘፍን; ሲውል በመዝሙ ሩ

መች ሰምቼ አውቃለ ሁ ; መቸስ አዳምጬ

እኔኑ በመስማት በድምፄ ተውጬ::

እና የኸውላችሁ

ድንቅ ነው ዘፈኔ::

5.የባከነ ሌሊት!

Aug 26, 2018 / በ በዕውቀቱ

ስዩም /

ወይ ሮንድ አላደርኩ

ወይ ኮኮብ አልቆጠርኩ

ወይ ደልቶኝ አልጨፈርሁ

ወይ ውስኪ አልተዳፈርሁ

የባለጌ ወንበር :ኮርቻ አልተሳፈርሁ

ወይ ሰአታት ቁሜ

ቤተክስያን ስሜ

ሰይጣን አላሳፈርሁ።

ሌቦች ደብድበውት

አንዱን ምስኪን ላሥር

ባምቢስ ድልድዩ ሥር

ቆስሎ የወደቀ

ገላው በላዩ ላይ :እንደጨርቅ ያለቀ

ፊቱ ተሸፍኖ : በደምና አቧራ

“በኡራኤል ርዱኝ ” ብሎ የሚጣራ

ምስኪን አባወራ

ብብት ሥር ገብቼ

አፋፍሼ አንስቼ

ተሸክሜ አድኜ

ስፈልግ አምቡላንስ :ሲሻኝ ዶክተር ሁኜ

ወይ ምግባር አልሠራሁ

ወይ ጀብድ አልፍፀምኩኝ : ወይ ፅድቅ

አላፈራሁ።

አንድ በትረ- ሙሴ

ሁለት ስስ አሎሎ

ከጭኔ መሀከል ሲያመሽ ተንጠልጥሎ

ሲባክን ዝምብሎ

” እሸኝ የኔ ጀግና እንደሰነፍ ቆሎ”

የምትል መለሎ

ልቤን ሳትሰውረው

አልጋየን ሳትሰብረው።

ወግ ቢጤ ሞንጭሬ: ፌስቡክ ላይ

ሳለጥፍ

” እናትዋን ጨረቃ” የሚል ግጥም

ሳልጥፍ።

አንዲት ሴት- አዳሪ :ቺቺንያ ምንገድ

ላይ

እድሉዋ ሰባራ :ሰውነቱዋ አማላይ

ካፍያውና እንባዋ : ተጋግዞ ሚያረጥባት

ደምበኛ ስትጠበቅ :ደመኛ ጥሎባት

አምስት ደፋሪዎች : ከበው ሲያዋክቧት

ሲገፉ ሲስቧት

” እረ በናታችሁ በወላድ ማህፀን

እህት የላችሁም?” ብላ ስትማፀን

ልመናዋ ስቦኝ

እንዳበጀ በለው : በደሏ አንገብግቦኝ

ከሁዋላ ደርሼ

ነበልባል ለብሼ: ነበልባል ጎርሼ

እንደብሩስሊ: እንዳየሩ ጋኔን

እግሬን ወንጨፍ ወንጨፍ

ወዝወዝ ወዝወዝ ጎኔን

በማረግ ቃኝቼ

ከሁዋላ ነው ሲሉኝ ከፊት ተገኝቼ

ካምስቱ መከከል አራቱን ነጥየ

ከቻልኩ በካራቲ ካልቻልኩ በሳቅ ጥየ።

ድል ሳላስመዘግብ

ውጥረት ሳለረግብ

ወይ ታሪክ ሳልሰራ - ወይ ታሪክ

ሳልዘግብ

ያለምንም ጣጣ : ያለምንም ፀጋ

አለሰበብ መሸቶ አለሰበብ ነጋ።

6.አይደለም ምኞቴ

/ በ በዕውቀቱ

ስዩም /

አይደለም ምኞቴ

ለምለም አንገትሽ ላይ : ክንዶቼን

መጠምጠም

ዳሌሽ ላይ መንሳፈፍ: ጭንሽ ማሃል

መስጠም

እይደለም ምኞቴ

ከንፈርሽን ማለብ

ቀሚስሽን መግለብ

ከገላሽ ቆርሼ :ገላየን መቀለብ

ደረትሽን ማለም

ጡትሽን መሳለም

በቁንጅናሽ ጅረት : ገነቴን ማለምለም

አላማየ አይደለም::

ምኞቴን ልንገርሽ?

ካለሺበት ቦታ: ቀልቤን ማሰማራት

ወትሮ ካንቺ ጋራ: ቡና መጠራራት

ሰላም መገባበዝ: ትዝታ መጋራት

የጨለመ ፊቴን : ባይንሽ ጮራ

ማድመቅ

በቃላትሽ መስከን: በሳቅሽ መጠመቅ

በጎ መንፈስሽን :ካይንሽ ላይ መሻማት

ርጋታሽን ማጥመድ : ዝምታሽን

መስማት::

7.ምንሽን

/ በ በዕውቀቱ

ስዩም /

የሰው አገር ሙጥኝ ብየ-በወጣሁበት

እንዳልቀር

ሀገሬ ፍቅርሽ ሳበኝ -ግና ምንድር ነው

ማፍቀር?

እንዳስመሳይ አዝማሪ -ካልሸነገልኩሽ

በቀር

ከተወለድሁ እስተዛሬ ከጣትሽ መች

ጎርሼ

ወተትሽን መች ቀምሼ

ወለላሽን መች ልሼ

ሲርበኝ

ጠኔ በቀኝ በግራ እንደ ጭፍራ ሲከበኝ

የት ነበር የንጀራሽ ሌማት

ሾላ ስለቅም ተሻምቼ ከሸመላ ከማማት

ኑሮየ ሁዳዴ ጦም ! ፋሲካ አልባ

ህማማት

እና ከድሎት አገር የሲሳይ ዶፍ

ከሚያወርደው

ምን ገፍቶኝ ነው በሞቴ ? ወዳንቺ

ምሰደደው

ምን ነክቶኝ ነው? ምንሽን ነው

የምወደው

እኔና ብጤዎቼ- እኛ ቅብዝብዝ ልጆችሽ

መስኮት በሩ ተዘግቶብን- ተበትነን

በደጆችሽ

ይሄው ሶስት ሺ ዘበን- ወደ ሰማይ

አንጋጠን

በንዝርት እግር ተንበርክከን -በቀይ እንባ

ስንማጠን

የእለት እንጀራችንን ነፍጎ- የለት

ገጀራችንን ሰጠን::

አሁንማ ለመከራሽ ማን አለና የሚገደው

እሪታሽን እንደዘፈን ያለም ጆሮ ለመደው

እና ምንሽ ነው ሚስበኝ ? ምንሽን ነው

የምወደው?

ዛሬም ሆነ ያለፈው

በላባ ብእርም ይሁን- በኪቦርድሽ

የተፃፈው

ታሪክሽን ሳነበው -ደምና አመድ ነው

የሞላው

መች ተነቅሎ ከወለልሽ -የሾህ ጉንጉን

አሜኬላው

መች ተጥሶ ያውቃልና -የጭቆናሽ

ዘመን ኬላው

ስልጣን ፈልሶ ቢሸጋገገር ካንዱ ጭራቅ

ወደ ሌላው::

እናም እንሆ!

ያለፈውን ዘመን ትቼ የቀረኝን እያሰላሁ

የብርሃን ቅሪት ባጣ አምፖሌን በተስፋ

ሞላሁ

እንጀራየን እንደ ሀሰንሊበዳበሳ

እየበላሁ::

ከዚህ ሁዋላ አልልሽም ወዴት አለ ያንቺ

አለኝታ?

ምንሽ ነው ግን የሚስበኝ ልማድ ይሆን

ወይ ይሉኝታ

እግሬን ከምድርሽ ጋራ ምንድነው

ያስተሳሰረው

ያገር ፍቅር አለኝ ብልስ- ምንሽን ነው

የማፈቅረው?

8. እሳት ወይ አበባ

(ሎሬት ፀጋዬ ገብረ መድህን)

ሌት ከዋክብቱ እንደ ፀደይ

አጥለቅልቆን በቀይ አደይ

ሰማዩ ሥጋጃ አጥልቆ

ተሸለምልሞ አንጸባርቆ

ፈክቶ አሸብርቆ ደምቆ

በአዝመራ በአጥቢያ ዐፀድ ሰፍኖ

የዓደይ አዝርዕት ተከሸኖ

በዕንቁጣጣሽ ሰብል ታጥኖ

ኢዮሃ አበባዬ ሆኖ፥

ጨረቃዋ ከቆባዋ፥ ከሸልምልሚት

እምቡጧ

ጧ ብላ ከሰንኮፈንዋ፥ ተንዠርግጎ

የእንኮይ ቡጧ፥

ድንግል ጽጌ-ረዳ ፈልቃ

ፍልቅልቂት ድምቡል ቦቃ ...

ተንሠራፍታ የአበባ ጮርቃ፥

ታድያን ብሌኑ የጠጠረ

ባሕረ - ሃሳቡ የከረረ

የውበት ዓይኑ የታወረ

ልበ-ሕሊናው የሰለለ

አይ፥ አበባ አይደለም አለ፤

አይ፥ እሳት አይደለም አለ፤

ያልታደለ። ...

ሰማይ ጨለማ ነው እንጂ፥ እሳት

አደል ብሎ ካደ

እቶን ባይኑ እየነደደ።

ከዋክብቱ እንደ ችቦ

በነበልባል ወርቀ ዘቦ

ከፅንፍ ፅንፍ አውለብልቦ

ደመራው እየተመመ

እየፋመ እየጋመ

ደመና እንደንዳድ ሲነድ

መንጸባርቅ ሰደድ ሲወርድ፥

በራሪ ኮከብ ተኩሶ

በአድማሳት እሳት ለኩሶ...

ይኸ እንደኔና እንዳንቺው፥ የውበት

ዓይኑ የሰለለ

ሰማይ ጨለማ ነው እንጂ፥ እሳት

እኮ አይደለም አለ፥

ያልታደለ። ...

...ይቅር ብቻ አንናገርም፥

እኔና አንቺ አንወያይም፤

ለውይይት አልታደልንም

እንዲያው ዝም፥ እንዲያው ዝም ...

ዝም።

አበባ አንሆን ወይ እሳት

ተጠምደን በምኞት ቅጣት

ሰመመን ባጫረው መዓት

ዕድሜ አችንን እንዳማጥናት፤ ...

እሳት አንሆን ወይ አበባ

በሕቅ እንቅ ስንባባ

ባከነች ልጅነታችን፥ እየቃተትን

ስናነባ

ሳንፈጠር በሞትንባት

ሳናብብ በረገፍንባት

ሳንጠና ባረጀንባት

አበባ ወይንም እሳት፥ መሆኑን ብቻ

አጣንባት።

1966 ዓ.ም.

ብርሀንና ሠላም ማተሚያ ቤት

9. የኢትዮጵያ ህዝብ መዝሙር

አሁን

የዜግነት ክብር በኢትዮጵያችን ፀንቶ

ታየ ህዝባዊነት ዳር እስከዳር በርቶ

ለሰላም ለፍትህ ለህዝቦች ነፃነት

በእኩልነት በፍቅር ቆመናል ባንድነት

መሰረተ ፅኑ ሰብዕናን ያልሻርን

ህዝቦች ነን ለስራ በስራ የኖርን

ድንቅ የባህል መድረክ ያኩሪ ቅርስ

ባለቤት

የተፈጥሮ ፀጋ የጀግና ህዝብ እናት

እንጠብቅሻለን አለብን አደራ

ኢትዮጵያችን ኑሪ እኛም ባንቺ እንኩራ።

በ1984 ዓ.ም

ግጥም፡-ደረጀ መላኩ መንገሻ፤

ዜማ፡- ሰሎሞን ሉሉ ምትኩ

"በዘመነ ደርግ"

ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ -ኢትዮጵያ ቅደሚ

በኅብረተሰባዊነት - አብቢ ለምልሚ!

ቃል ኪዳን ገብተዋል - ጀግኖች ልጆችሽ

ወንዞች ተራሮችሽ - ድንግል መሬትሽ

ለኢትዮጵያ አንድነት - ለነፃነትሽ

መስዋዕት ሊሆኑ - ለክብር ለዝናሽ!

ተራመጂ ወደፊት - በጥበብ ጎዳና

ታጠቂ ለሥራ - ላገር ብልጽግና!

የጀግኖች እናት ነሽ - በልጆችሽ ኩሪ

ጠላቶችሽ ይጥፉ - ለዘላለም ኑሪ።

በ1968 ዓ.ም

ግጥም፡-በአሰፋ ገብረማርያም

ዜማ፡-አቶ ዳንኤል ዮሐንስ

"በንጉሱ ዘመን"

ኢትዮጵያ ሆይ ደስ ይበልሽ

በአምላክሽ ኃይል በንጉስሽ

ተባብረዋልና አርበኞችሽ

አይነካም ከቶ ነፃነትሽ

ብርቱ ናቸውና ተራሮችሽ

አትፈሪም ከጠላቶችሽ።

ድል አድራጊው ንጉሣችን

ይኑርልን ለክብራችን።

**

በ1919 ዓ.ም

ግጥም፡-- በቀኝ ጌታ ዮፍታሔ ንጉሤ

ዜማ፡-- ኬቨርክ ናልባልድያን

11.

"ይታዩኛል ብዙ ሰዎች

ዕራፊ አልባ፣ ልብስ የለሾች፤

ይታዩኛል ብዙ ልብሶች

በውስጣቸው የሉም ሰዎች።"

~ ሩሚ

(ትርጉም ኄኖክ ስጦታው)

12.

(በላይ በቀለ ወያ)

አልጋ ባልጋ ሆኖ ፥

የጥንቸሎች ፍጥነት ፍጥነት ከተባለ፣

በዔሊዎች ጫንቃ ፥

ራሱን ያልቻለ ግዙፍ ድንጋይ አለ።

ያንን ግዙፍ ድንጋይ፥

ከዔሊ ጫንቃ ላይ ላፍታ ቢነሳላት፣

ከጥንቸሎች ፍጥነት ፥

አስር እጅ የሚሻል በቂ ፍጥነት አላት።

ያንን ግዙፍ ድንጋይ ፥

ለዘመናት ቀርቶ ለሰዓታት ያህል ጥንቸል

ብትሸከም፣

መሮጡ ይቅርና ፥

መራመድ አትችልም ነፃ ባልሆነ ዓለም።

ፍትህ በጎደለው ነፃ ባልሆነ ሀገር፣

ድንጋይ ተሸክሞ ፥

የፈጠነ የለም ከዔሊ በስተቀር።

ፍትህ በሞላበት ነፃ በሆነ ሀገር፣

ይቻላል ቀላል ነው ክንፍ አውጥቶ መብረር።

13. ዋ!

(በረከት በላይነህ)

አይኔ ወደደሽ ስልሽ፣

አይኑን አጥፋው ብለሽ ገባሽ አሉ

ስለት

ምኞትሽ ሰመረ አይኖቼ ጠፉልሽ ይኸው አንደዘበት።

ግን መች ተውሻለው

በልቤ ብሩህ አይን ዛሬም አይሻለው።

ደሞ አንደዚ ስልሽ አትወጅኝምና

ልቡንም አጥፋልኝ ብለሽ ትሳይና

ፀሎት ያልቅብሻል እሞትብሽና።

14. "ያልተማረ ይግደልህ"

ትናንትን አፈቀርኩት" ዛሬን ግን ጠላሁት

አፌን ለሆድ ብቻ ሲጮህ አገኘሁት።

ትንሽ መግፋት ቢቻል ጊዜን ወደ ኋላ

እኔስ በተሰየምኩ ካባቴ ፊት ለፊት ከአያቴ በኋላ

ወይ ታሪኬ ሊፃፍ ወይ ግፌ ሊሰላ።

አባባ ገድልህን ለምን ነው የነገርከኝ?

ለትናንት አሻቅለህ ዛሬ አስጠላኸኝ

ብትከፍተው ገለባ

ሕይወት ትግል አልባ፣ ትግሉም ሕይወት አልባ

የተማረ ይግደለኝ ብለህ አጓግተኸኝ

ፊደል ከቆጠረ ቁጥርን ከደመረ ለሆዱ ካደረ

መንጋ መሀል ጣልከኝ

እኔም ተማከርኩልህ" ተመራመርኩልህ

የመብት አቡጊዳ ትግሌን ጀመርኩልህ

መብሌን አትንኳት ብዬ ፎከርኩልህ

ኧረ በሞትኩልህ

ይልቅስ ልንገርህ" ሞትክን በተማረ መመኘትክን እርሳው

ጽድቁን ከፈለግከው

ፊደል ያልቆጠረው ያገሬ ገበሬ ተኩሶ ይጣልህ፣ ይግደልህ

ከማሳው።

(ቼበለው መኩሪያ፣ ማለዳ፣ 1993)

15. "በድንቅ አብቃይ ምድር"

አገሩ በሙሉ፣ የብስና ባህሩ፣ ውሃ ሰራሽ ሆኖ

ለምን ያስቡታል? ዓባይን ለመስኖ

ለእኛ አልተሰጠንም? ዓለምን መመልከት፣ ከጥቅም ነጥሎ

ውሃ ተሸምኖ፣ ባዬር ሲተጣጠፍ፣ ማዬት ዝም ብሎ

ሃሳብን ማሳረፍ፣ ከማር ከሰም ስሌት

ለእኛ አልተሰጠንም? ማዳመጥ፣ ማጣጣም፣ የንብን ማህሌት

ዶሮን ከዶሮ ወጥ ነጥሎ መመኘት

ለሣታዊ ክንፉ፣ ለንጋት መዝሙሩ፣ ላጫጫር ምስጢሩ፣ ቃል

መርጦ መቀኘት

ፈልጠው ሳይማግዱን፣ ወይም ሳይዳስሱት፣ ከስሩ ሳይሰግዱ

ዋርካ አይደነቅም? በእንግዳ ህላዌው፣ በቅጠል በንግዱ?

መልስ የለም

መልስ የለም።

ከጢስና ውሃ የተሰራ ሸማ፣ ባዬግ ይታጠፋል፣

ንቡም ይዘምራል፣ ዶሮውም ይጭራል፣ ዋርካውም በጆቹ

አየሩን ይቀዝፋል

የማይገርመው ትውልድ፣ በድንቅ አብቃይ ምድር፣ እየኖረ ያልፋል።

(በእውቀቱ ስዩም፣ የሣት ዳር ሐሳቦች)

16. "ያገረሸ ፍቅር"

(ገብረ ክርስቶስ ደስታ፣ መንገድ ስጡኝ ሰፊ፣ 1998)

የሰማይ

አሞራ

ላዋይህ

ችግሬን።

ብረር ሒድ ንገራት”.

ከትልቁ

ዛፍ

ሥር፣

ዱሮ በልጅነት

ከተጫወትንበት

ከትልቁ ዛፍ ሥር አታጣትም ፍቅሬን

ብረር

ሒድ ንገራት፣

ንገር መናፈቄን፣

17. "ጠብቄሽ ነበረ"

(ደበበ ሰይፉ፣ ለራስ የተጻፈ ደብዳቤ፣ 1992)

መንፈሴን አንጽቼ

ገላዬን አጥርቼ

አበባ አሳብቤ

አዱኛ ሰብስቤ

ጠብቄሽ ነበረ፤

ብትቀሪ ጊዜ፣

መንፈሴን አሳደፍኩ

ገላዬን አጎደፍኩ

አበባው ደረቀ

አዱኛው አለቀ፤

ብትቀሪ ጊዜ፣

የጣልኩብሽ ተስፋ

እኔን ይዞ ጠፋ።

18. “ኢትያጵያዊው ዘኬዎስ!”

(በላይ በቀለ ወያ)

እኔ እንደ ዘኬዎስ ቢያጥርብኝ ቁመቴ

ጌታ አንተን ለማየት፤ ዛፍ ላይ

ከመውጣቴ

“ና ውረድ ከዛፉ

እራት ካንተ ጋር ነኝ እንዳትለኝ አምላክ!

ከመውረዴ በፊት

እራት እንድትበላ፤

በቤቴ ያለውን ባዶ ሌማቴን ባርክ።

19. “ፍቅር የያዘው ሃብታም የጻፈው ግጥም”

(በላይ በቀለ ወያ)

“እመጣለሁ ብለሽ” ከቀጠርሽኝ ቦታ

ዕድሜ እንደ “ቅጽበት” ዘመን እንደ

“አፍታ”

ቆሜ ስጠብቅሽ፤ ሳላገኝሽ ያልፋል

ስትቀሪ ጊዜ

ዘላለሜ ባክኖ፤ ናፍቆትሽ ይገዝፋል።”

ምናምን እያለ

በቃል አሳምሮ፤ የሚጽፍ ብሶቱን

ደሃ ገጣሚ ነው፤ ልንገርሽ እውነቱን

እናልሽ የኔ ውብ በፍቅርሽ ተቃጥላ፤

ነፍሴ ብትቀልጥም ቆሜ ስጠብቅሽ

ዕድሜዬ አያልፍም፤ ዘመኔ አያመልጥም

ባለሽበት ቦታ “ ሳልቀጥርሽ ላግኝሽ”፤

20. "ነጠብጣብ ሐሳቦች"

(በእውቀቱ ስዩም፣ የ፣ሣት ዳር ሐሳቦች፣ 2000)

ሰማይ ከሚመክን ይፀንስ መከራ

ያርግፍ" ያርግፍ" ያርግፍ" መአት እያፈራ

የ፣ሣት ዛፍ ባለበት ሰደድ ላያስፈራ።

ከሐምሌት ጋር ሞቷል፣ የማመንታት ዓለም

ከሆኑ በኋላ፣ አለመሆን የለም፤

ሸክም ፀጋ ሆኗል ፀጋህን አትግፋ

በጠባብ ዓለም ውስጥ ትከሻህን አስፋ።

አንድ ህልም እንደ ጠጅ፣ እየደጋገሙ

ንግር፣ ትንቢት ሳይሆን ታሪክ እያለሙ

ተኝቶ መነሳት

አቤት ሲያቅለሸልሸ

ጌታ ሆይ አትንሳት

ነፍሴን እንቆቅልሽ።

21. "ለምንድነው የማትወጂኝ"?

(በፀጋዬ ደባስ)

"በዚህ ሁሉ ዘመን ሩጫ ጥረቴ

ሌላ ምን ሀብት አለኝ አንቺ ነሽ ንብረቴ"

ሳዜም እየኖርኩኝ

ከደም አጥንት አይደል ፍቅር ነው ስሪቴ

ሀሜትሽ ነደደኝ ልለኩስ ትምባሆ

ወዴት ነሽ ክብሪቴ

ለምንድነው የማትወጂኝ?

አሁን መቼ ለታ ቢራ እየተጎነጨን

ጎደኛሽ ስትመጣ እየሳምሺኝ ጉንጩኔ

"ተዋወቂው ውዴ የሰማኒያ ባሌ ነው"

ስትያት ስሰማ "ሀያውስ የማነው"?

ብዬ ብጠይቅሽ

ከዝምታ በቀር ምን ነበረ መልስሽ?

እኔ ማለት እኮ.....

እገሌን ለማድነቅ እገሌን የማልንቅ

ጎሳዬ ተስፋዬን እንጂ ጎሳዬን ማላዳንቅ

ለብሄራዊ ቡድናችን ውጤት

ቅንጣት ማልደነግጥ

ብሄራዊ ባንካችን ግን ያሳስበኛል በርግጥ

ከውጪ ወገን ኖሮት ዳላር ካላሻገረ

ይቆጥቡ ይሸልሙ

በይቀበሉ ይሸለሙ ተሻረ?

ተይው አትውደጂኝ.....

አውቃለው ተራ ሰው ነኝ ባድናቆት ያልናኘው

በስሜት ፍትጊያ እንጂ በስለት ያልተገኘው

ቢሆንም ቢሆንም

እኔን ላለማፍቀር ምክንያት አይሆንም

ተይው አትውደጂኝ ልብሽ ይሞግተኝ

እኔ መፃተኛው ሌላው ሌላው ቢቀር

ስለማውቀው ገላ መግጠም አያቅተኝ።

22. መራራቅ

በረከት በላይነህ (የመንፈስ ከፍታ)

.

ቅዠታም አዳሩን

ጨፍጋጋ ውሎዉን

ዝብርቅርቅ ተስፋውን

ደረቅ ትዝታውን...

በይሉኝታ ከፈን እየጠቀለለ

ከጥርሱ ሲጥለው

ተቀባይ ይሻማል ሳቅ እየመሰለው።

23. ያልጣዱት አይበስልም

(በእውቀቱ ስዩም)

ፍቅር እንደ ዝናብ ከሰማይ አይወርድም

ያበባ መደብ ነው

በሰው የሚታነፅ : በሰው የሚወድም

ተዘርቶብን እንጂ :ተሰብከን አንወድም::

"ወዳጄ ወዳጄ " የሚያቀነቅኑ

አገር ያቀኑ ለት መች ልብን አቀኑ

ሳይወጡ ሳይወርዱ

ውብ ስራን ከውብ ቃል :ሳያስተባብሩ

ከድሜ እና ከምቾት ቆርሰው ሳይገብሩ

ፍቅር መች ይፈልቃል?

በስብከት በምልጃ በየዋህ ሰዎች ህልም

ያልጣዱት አይበስልም

ያልዘሩት አይበቅልም::

24. ይነጋል!

(በረከት በላይነህ)

ታድለሻል ቢሉም፣

የ13 ወር ፀሀይ፣ የ13 ወር ፀጋ

ብርሀንሽ ተሰርቆ፣

ሲጨላልም እንጂ፣ መች አየን ሲነጋ?

ተፈጥሮ ቸር ሆና፣

ሰማይዋ ባይነጥፍ፣ ምድሯ ቢለመልም፣

ከልጆቿ ልብ ውስጥ፣

ፍቅር ሲጎድል ነው፣ ሀገር የምትጨልም!፣

"አረ ነግቷል" ቢሉ የታለ የነጋው?

አዕላፋት ተቧድነው፣ በየጎጥ በመንጋው፣

ሰው ከነገ ይልቅ፣ ዛሬን እያሰጋው የታለ የነጋው?

ታሪኩን እንዳይፅፍ፣ ትውልድ እጁ ታስሮ፣

በትላንቱ ሾተል ዛሬው ተሸንቁሮ፣

ባልኖረው ተካሶ፣ ባልሰራው ተዋቅሶ፣

ለፀብ መዶለቻ፣ ያሆቱን ስም ጠቅሶ፣

ላለፈው ሲናከስ ለመጪው ሳይተጋ፣

በምን ስሌት ይሆን፣

ትዉልዷ ጨልሞ ሀገር የምትነጋ?

የህሊና መስታወት በጥበብ ሲፀዳ፣

ማስተዋል እንዳሆደይ ፈክቶ ሲፈነዳ፣

መገፋፋት ሲቀር ፣መደጋገፍ ነግሶ

አንዱ ማገር ሲሆን፣ ሌላኛው ምሰሶ፣

የአብሮነትን ሸማ ትዉልዱ ሲሸምን፣

ያኔ ነው ሀገሬ መንጋቷን የማምን።

25. <<ደሞዝ ወጥቷል>> የሚል፥

ሜሴጅ የገባ ቀን፥ እንዲህ ያደርገኛል

(በላይ በቀለ ወያ)

አዝዜ ልጎርሰው፥

ያጠቀስኩት ሸሮ፥ አፌን ገፍቶ ይርቃል

ማባያ የሰነግኩት፥

አረንጓዴ ቃርያ፥ በቅፅበት ይደርቃል

እንደ በረኃ ምድር፥

እንጀራዬ ከስሎ፥ ይሰነጣጠቃል።

ጆሮዬ ከፒያሳ፥

ቦሌ እሚንቆረቆር፥ ይሰማዋል ድራፍት

አይኔ ካራት ኪሎ፥

ቄራ የሚፈረሽ፥ ይታየዋል ፍትፍት።

<<ደሞዝ ወጥቷል>> የሚል፥

ሜሴጅ የገባ ቀን፥ እንዲህ ያደርገኛል

ያበዳሪን ሰፈር፥

በጀግና አረማመድ፥ ሄዳለሁ ሰንጥቄ

የቡቲኩን ጌታ፥

የጃኬቱን ዋጋ፥ አልፋለሁ ጠይቄ

ስቸስት የከዳኝ፥

ወዳጄን ፈልጌ፥ አልሳለሁ ጥፊ

እንዳያዩኝ ብዬ፥

ከተደበቅኋቸው፥

ካሜራዬ ጋራ፥ እነሳለሁ ሰልፊ።

<<ደሞዝ ወጥቷል>> የሚል፥

ሜሴጅ የገባ ቀን፥ እንዲህ ያደርገኛል

ኤድናሞል ደጃፍ፥ ላይ እንጎራደዳለሁ...

ቮድካ እንኳ ባይገኝ፥

የሜንት ያሸሬቲቭ፥ ቦትል አወርዳለሁ

ባለረዥም ፀጉር፥

ባለ ለስላሳ ድምፅ፥ ባለ አይን ባለ አንገት

እያልኩ የተውኳቸው፥

የቸከሶቼ ስልክ፥ ትዝ ይለኛል ድንገት።

ፀሃይ ሲያዘቀዝቅ፥

እያንገሸገሸኝ፥

እያንቀጠቀጠኝ፥ ፀጥ ያለው ሰፈሬ

ወደ ሃያሁለት፥

ቦሌ መድሃኒያለም፥

ወደ አትላስ ጀርባ፥ይመራኛል እግሬ።

<<ደሞዝ ወጥቷል>> የሚል፥

ሜሴጅ የገባ ቀን፥ እንዲህ ያደርገኛል

26. የቅዳሜ ማስታወሻ

(በላይ በቀለ ወያ)

ልባቸውን አይቶ

እግር የነሳቸው ፣ ቀርፋፋ ቀናቶች

ዘልዛላ ለሊቶች

እንደ ማቱ ሳላ ፣ እድሜ የሚያዘግሙ

ከሰኞ ተነስተው ፣ አርብ እስከሚያከትሙ

በስራ በትምህርት

በስብሰባ ብዛት

በሰበብ ባስባቡ ፣ ሲያቀጥኑኝ አክርረው

እንደ ጠቦት ቆዳ ፣ ሲሰቅሉኝ ወጥረው

በአማራሪ ቀኖች ፣ የማልማረረው

እራሴን ለማጥፋት

ብዙ ጊዜ አስቤ ፣ ሀሳብ ምቀይረው

ለቅዳሜ ስል ነው።

ዛሬ ቅዳሜ ነው ፣

አደረች አራዳ ፣ ዘፈን ይለቀቃል

አሳዳሪ አራዳ ፣አልጋቤቱ ያልቃል

እንደጉድ ይጠጣል ፣ ይሰከራል በጣም

ነይና ላሳይሽ

ቅዳሜ የቀረ ፣ ዘላለም አይመጣም።

ዛሬ ቅዳሜ ነው

በየመጠጡ ቤት ፣ ገርበብ ያሉ ጭኖች

በየ ጎዳናው ላይ

ቆንጆ ሴት የጫኑ ፣ ጢኒኒጥ መኪኖች

በየ ፋርማሲው ቤት

ፅንስን የሚያመክኑ ፣ እንክብል ኪኒኖች

የሚያዘዋውረው

የሚመነዝረው

የሚያመነዝረው ፣ እንደጉድ ይበዛል

ፌስቡክ ላይ ምታውቂው ፣

በስካር ጠንብዞ

ፖስት የሚያደርገውን ፣ ሚሪንዳ ይገዛል

"ይህች ሀገር ወዴት ነው

የምትሔደው? " ፣ ብሎ ላይኩን ያባዛል።

::::::

ነይና ላሳይሽ

ጨዋ የሚባል ህዝብ ፣ ጠፍቶት ትርጓሜ

ቀሚስ የሚባለው

የት እንደሰረሰ ፣ አጥሮ እንደጿግሜ

የዝች ሀገር ጉዞ

ወዴት እንደሆነ ፣ መልስ አለው ቅዳሜ።

ነይና ላሳይሽ

የአልኮል ባህር ላይ ፣ የመረብ አጣጣል

መንግስት አልወርድ ያለው

ውስኪ እያወረደ ፣ ሴት ከቦት ይጠጣል

የቢራ ያጣ ሰው

ስለውስኪ አጠጣጥ ፣ አቃቂር ያወጣል

ጭፈራው ለጉድ ነው ፣

ጨፋሪው ብዙ ነው ፣ አያስጥልም ጠጠር

ዝቅ ቢሉ ጭን ነው

ጎንበስ ቢሉ ጡት ፣ ቀና ሲሉ ከንፈር

ነፃ ይታደላል

አንድ የሰከረ ሰው

እቺ ሀገር ወዴት ነው ፣ የምትሔደው ይላል።

ሁሉ እየተነሳ

ይቺ ሀገር ወዴት ነው

የምትሔደው ብሎ ፣ መጠየቅ ቢወድም

ነይ መልሱን ላሳይሽ

ወደ አልጋ ቤት እንጂ ፣ ወዴትም አትሔድም።

ዛሬ "ቅዳ" ሜ ነው

27. ቱ! በል

[አሰፋ ጉያ ‹‹የከንፈር ወዳጅ››(1984)]

ቱፍ - በል! ማሙሽ ቱ!

አለችው እናቱ

እሷው ናት አባቱ

ወንድምና እህቱ

ነፍስና አካላቱ::

ማሙሽ ብቻ - ብቻውን

እያዩ መምጫ - መምጫውን

ያለምንም ከልካይ

ከጐጆው በራፍ ላይ

አፈር አድበልብሎ

ሲቅም እንደቆሎ...

እናት በችኮላ

እንስራዋን አዝላ

ልጄ! ...ልጄን! ...ብላ

አሳብራ መንገዷን

ዘንግታ ድካሟን

ስትደርስ ከደጃፉ

ሆኖ ስታገኘው አፈር ቅሞ ባፉ

ብድግ አ'ረገችው

ቱፍ - በል!!! እያለችው::

ጭቃ ባፉ ሞልቶ ...

መላ - አካሉ ቦክቶ ...ሆኖ ስላየችው፤

መታ አ'ረገችው

ቱፍ - በል! እያለችው::

እንባውን ስታየው

ቱ - በል! እያለችው

እየዳበሰችው

እያባበለችው

አቅፋ እየሳመችው

አዝላ እያስተኛችው

እሷም እንደማሙሽ ጭቃውን ቃመችው::

28.

ተቃቅፈን ስንሄድ ለሚያገላግሉ

ጉንጭሽን ስስምሽ ነከሳት ለሚሉ

:

ከፍቅራችን ይልቅ ጸብ ለናፈቃቸው

ከራስሽ ተጣልተሽ...

የወሬ ማድመቂያ ሰበብ አትሁኛቸው

አቤላ

29. እድሜ ለሷ!!!!!

አየሁ ራቁቷን

ውበቷን

እሳቷን

ልቤ በጣም ፈራ ድፍረቴ መከነ

ከጭኖቼ መሐል ድንኳን ተደኮነ

ና ትላለች ባይኗ

ሚሳኤል ጡቶቿን ተፊቴ ደግና

ፈራሁ ጠፋኝ አቅም

ከራዲዮኔ ውጭ ጡት ጠምዝዤ አላውቅም።

ከምኔው አቀፍኳት ከንፈሬ ራሰ

ቋሚው ብቻ ቀርቶ ድንኳኔ ፈረሰ

ከምኔው እሳቷን አቀፍኩት እስክነድ

እንዴት በዚህ ፍጥነት ተሰራሁ እንደወንድ

በውበቷ ገዳም ገባሁኝ ምናኔ

አጎንባሹ ቀናሁ ለቀሪ ዘመኔ

ፍቅሯን በገሞራ ለውሳ ቀይጣ

ወንድ አርጋ ሸኘችኝ ሰራችኝ አቅልጣ።

30.መኖርና ተስፋ

© በበድሉ ዋቅጅራ.

.

ለእራት ከተቀመጥን .. . . .

ከጨለመ ቀኑ፣

ቢሸሽም ዘመኑ፤

የለኮስኩት ሻማ፣ አልጠፋም መብራቱ፤

ለእራት የቀረበው፣ ሙሉ ነው ሌማቱ።

.

ለእራት ከተቀመጥን .. . . .

ከጨለመ ቀኑ፣

ቢሸሽም ዘመኑ፤

ጽጌረዳ አበባ፣ ከውሀ የዶልኩት፤

እንዲያ እንደፈካ፣

እንዲያ እንዳበበ፣ . . . ያው እንዳስቀመጥኩት፤

ጠረጴዘው መሀል፣ ከውሀው ውስጥ አለ፤

ጊዜን አስገብሮ፣ ውበት እያደለ።

የሾምኩት የወይን ጠጅ፣ ከገበታ መሀል

እንደተገተረ፤

ሲቀዳ እየሞላ፣

አመታት አለፉ፣ ጣእሙ ጨመረ።

.

.

ባንቺ ነበር ለካ፣

ጊዜዬ የሚሰፈር፣ አለሜ የታቀፈ፤

ካጠገቤ ሳጣሽ፣

ያ ዘላለም ምሽት፣ በሰከንድ አለፈ።

.

31. ቀረሽ እንደዋዛ

(ገብረ ፡ ክርስቶስ ፡ ደስታ)

፧

እንደ ፡ ድመቶቹ ...

የትም ፡ እንደሚያድሩት

እንደ ፡ ስልክ ፡ እንጨቶች ፣

እንደ ፡ ዛፍ ፡ ሀረጎች ፣

እንደ ፡ ቤት ፡ ክዳኖች ፣

ብርድ ፡ አቆራመደኝ ~ ስጠብቅ ፡ ስጠብቅ

ፆትመጫለሽ ፡ ብዬ...

ሳይ ፡ ማዶ ፡ ሳይ ፡ ማዶ ፣

የልጅነት ፡ ዐይኔ ፡ ሟሟ ፡ እንደ ፡ በረዶ፰

ትመጫለሽ ፡ ብዬ ፡ ደቂቃ ፡ ስቆጥር ፣

ትመጫለሽ ፡ ብዬ ፡ ደቂቃ ፡ ስቆጥር ፣

ትመጫለሽ ፡ ብዬ ፡ ባዝን ፡ ባንጎራጉር ፣

ትወጫለሽ ፡ ብዬ ፡ በበራፍሽ ፡ ብዞር ፣

ብርድ ፡ አቆራመደኝ ፣

የመንገድ ፡ መብራቶች ፡ አይተው ፡ አፌዙብኝ ፣

ውርጩ ፡ ቀለደብኝ ፣

ጨለማው ፡ ሳቀብኝ ።

አለመምጣትሽን ፡ አውቀዋል ፡ ያውቃሉ ፣

መስኮቶች ፡ ጨልመው ፣

ቤቶች ፡ ተቆልፈው ...

ከተማው ፡ ሲተኛ ፡ አይተዋል ፡ ያያሉ ፣

አለመምጣትሽን ፡ አውቀዋል ፡ ያውቃሉ ።።

⋮

32. "ውሻሽን እሰሪው"

አቤል ሽመልስ አቤላ

አንቺን ስመለከት እንቅፋት መትቶኛል

መምጫሽን ስጠብቅ ጸሃይ አጥቁሮኛል

ባጥር ላይሽ ብዬም ውሻችሁ ነክሶኛል

ያውም ክፉ ውሻ...

መምጫው ሳይታወቅ አድብቶ ሚያጠቃ

ግዳይ መሬት ጥሎ የሚለውስ ጭቃ

እቺን ስንጥር እግሬን ከአፉ አስገብቶ

አንከብሎኝ ሄዷል እመሬት ጎትቶ

ውሻሽን እሰሪው...

ይህን ሃይለኝነት ከማንስ ተማረ አሳዳጊው አንቺ

አትንኩኝ የምትይ አመል የነፈገሽ ለሰው

ማትመቺ !!

33. እየጠፉ...መብራት"

(ዳዊትሟጉሡ)

.

አ ት መ ጻ ደ ቂ!

.

ዙሪያሽን ቢከበው

ቀጣፊሽ በሙሉ..ላይ መልክሽን አይቶ

ቀን ያመጣው ተጓዥ

ገበያውን ሊያደምቅ...መድመቅሽን ሸቶ

.

.....ሲጠብቅ አድብቶ

ይልቁን ጠርጥሪ.!

ልጣጭ ቢጣል እንጂ አያውቅም ተበልቶ

.

.

ምን ላይን ቢያስጎመዥ...የበሰለ ፍሬ

መብሰል አይደለም ወይ የመትላት ጅማሬ?

.

ከአካልሽ በፊት

ገፍቶ ከሚጥልሽ..ለጊዜ ነጣቂ

አለት መሰረትሽን ውስጥሽን አድምቂ።

.

.

ይልቁኑ...ጠርጥር!

.

ከስንዴዎች መሀል

ያንተ ዛላ ረዝሞ፤ከክበብህ ሲገዝፍ

ዙሪያህን ተመልከት...ያለ መጠመድህን

በወፍ.... ወይ.....በወንጭፍ

.

መጠመድ ደግ ነው

ስንቱ ወጥቷል ከፍታ እንዳቀረቀረ

ወዴት ይሸሹታል?

ወገብን የሚመታን እያነጣጠረ

.

ይልቅ መጠርጠር ጎን

ደጅህ 'ሚካድሙን..."ፀሐይ ነህ" እያሉ

በውዳሴ ስለት

እየገዘገዙ በቁም የሚገድሉ

.

.

ድምቀትህን አይቶ

ህዋው ሁሉ ሲፈልስ...አጀብህ ሲበዛ

ጸሐይህን ወስደህ

ከዓለም ነጻ ወጥተህ...ራስህን ግዛ።

.

.

አመክንዮ አልባ ሳቅ

መንደሩን ሲወርሰው

ከግብራችን በልጦ..ከቀናችን ደምቆ

ይልቁን እንጠርጥር!

"እብደት እና ውሃ..ሲወስድ አሳስቆ"

.

የቃል አባይ ዶግማ...ሚዛን እየደፋ

መገፋትን ሲወልድ..የአማኒነት ምሱ

አመክንዮ ያጣ

ባዶ ሲሆንብህ...የጥያቄህ መልሱ

.

ዝም ብለህ ጠርጥር

ምላሽ እስኪያመጣ..መጠርጠር በራሱ።

.

(አሜን እንዲህ እናምናለን...ያመነውንም

እንጠረጥራለን።)

34. ሲሳይ ነው

(በላይ በቀለ ወያ)

.

.

ይመስለኛል በህልሜ...

ሰው ህልሙን ሲነግረኝ ፣ እኔ አንቀላፍቼ

ህልም እየፈታሁ ነው ፣ ህልሜን ማለም ትቼ።

.....

‹‹ይመስለኛል በህልሜ...

የተማረ ልጄ ፣ የተመራመረ

ባላዋቂዎች ፊት...

ያወቀውን ያህል ፣ ስለተናገረ

‹‹ተናገርኸን›› ብለው ፣ ሲገርፉት ሲገርፉት

‹‹ዝም››ያላቸው ጊዜ...

‹‹ንቆን ነው›› በማለት ፣ ባንድ ጥይት ደፉት::››

ብላ ስትነግረኝ ፣አንዲት ምስኪን እናት

‹ሲሳይ ነው መገረፍ ፣ ሲሳይ ነው መደፋት››

በማለት ስሸኛት ...

የታሰረ ህልሟን ፣ በህልሜ ፈትቼ

ህልሞች እየፈታሁ

ህልም እያየሁ ነበር ፣ ህልሜን ማለም ትቼ::

.....

‹‹ይመስለኛል በህልሜ...

የምወዳት ፍቅሬ ፣ እሷም ምታፈቅረኝ

ካገር ተሰደደች ፣ መሄዷን ሳትነግረኝ::››

ብሎ ለነገረኝ ፣ ላንድ ምስኪን ወጣት

‹‹ሲሳይ ነው መሰደድ ፣ ሀገር ለቆ መውጣት››

ብዬ እንደነገርሁት...

የታሰረ ህልሙን ፣ በህልሜ ፈትቼ

ሰው ህልሙን ሲነግረኝ...

ህልሜን ሳላይ ነጋ ፣ ከእንቅልፌ ነቅቼ::

.....

ከነቃሁነ በኋላ...

ማንም ህልሙን ይዞ፣

‹‹ፍታልኝ›› አይበለኝ ፣ ካለሁበት ቦታ

መታሰርም ቢሆን ፤ ሲሳይ ነው ሲፈታ!!!

::::::::

35. ቆንጆ ነኝ

(በላይ በቀለ ወያ)

.

.

ስላንቺ ቁንጅና

ስላንቺ ቁመና

ከንፈር እና ዳሌ

ጥርስና ተረከዝ ፣ ፀጉር ገለመሌ

ለጡት ለወገብሽ ፣ ለፀባይሽ ጭምር

በግጥም በዝርው ፣ ባድናቆት ስዘምር

እስከዛሬ ድረስ...

ውበትሽን አግንኜ ፣ ሰርክ መለፈፌ

እኔ ስለራሴ ...

አንዳች ቀን እንኳን ፣ ግጥም አለመፃፌ

ሲትጠዪኝ ቆጨኝ

ቢሆንም ቆንጆ ነኝ።

::::::::::::::::::

እርግጥ ነው ብዙዎች...

ስለኔ ሳወራ ፣ ድንገት ያኮርፉኛል

ያንተን ሌሎች ያውሩ ፣ ብለው ይነግሩኛል

እኔን ከኔ በላይ...

እርግጠኛ ሆኖ ፣ ሌላ እንዴት ያውቀኛል?!

:::::::::

እናም እኔ ማለት...

ቁመቴ ከአክሱም ፣ በእጥፍ ይረዝማል

ጣፋጭ አንደበቴ...

መስማት ለተሳነው ፣ ለስልሶ ይሰማል

ውብ አረማመዴ...

እንኳን መንገደኛን ፣ መንገድን ያቆማል።

::::::

የከንፈሬ ወዙ ፣ ጥፍጥናው አያልቅም

ጥርሴ ሺ ገዳይ ነው!

ሺ ሟች ላለማየት ፣ ኗሪ ፊት አልስቅም።

ከአይኔ ብሌን ውስጥ ፣ ብርሐን ይፈልቃል

አይኔን ያየ ሁሉ

ልቡን አሳውሮ ፣ በፍቅር ይወድቃል።

:::::

የገላዬ ጠረን ፣ ከሽቱ እጥፍ ነው

መልካም ጠረን ሁሉ...

አለ ባሉት ስፍራ ፣ እኔ አለሁ ማለት ነው።

ፀባየ ትሁት ነኝ ፣ ምጡቅ ነው እውቀቴ

ግርማ ሞገሳም ነው ፣ ተክለ ሰውነቴ

ያየኝ ይወደኛል

የወደየኝ ሁሉ ፣ መቼም አይጠላኝም

ከዚ በላይ እንኳን...

ብዙም ስለራሴ ፣ የማውቀው የለኝም።

እንደውም እንደውም...

አልጎርርም እንጂ ፣

ያፈር ሰውነቴን ፣ በቁንጅና አብየው

ቆንጆ ማየት ሲያምረኝ ፣ራሴን ነው ማየው።

ብቻ ግን ቆንጆ ነኝ!!!

36. እየሔዱ መምጣት

(በላይ በቀለ ወያ)

.

.

አንዴ ነው ይሉኛል ፣ በፍቅር መጎዳት

አንዴ ነው ይሉኛል ፣ ባመኑት መከዳት

እኔ ግን አላምንም!

ካለፈ ህይወቴ ፣ አላውቅም ተምሬ

አውቃለሁኝና

ብዙ ተጎድቼ ፣ ብዙጊዜ አፍቅሬ።

በፍቅር መንገድ ላይ ፣ ተክዤ ተጉዤ

የማውቃቸው ሁሉ

የሸለሙኝን መልክ ፣ ጠባሳ ልብ ይዤ

አንቺ ጋራ ስደርስ...

ልብሽና ልቤ ፣ እንደተሳሳበ

እንዳዲስ ሳፈቅር...

ወደ ነፍሴ ምድር ፣ ጥያቄ ዘነበ።

ቆይ ስንቴ ነው መውደድ ፣ ስንቴ ነው መጎዳት

ቆይ ስንቴ ነው ማመን ፣ ስንቴ ነው መከዳት?

ለስንት ግዜ ነው

እርሜ ነው እያሉ ፣ ያለ እርም ማፍቀር

ስንቴ ነው መታቀፍ ፣ ስንቴ ነው መገፍተር?

ለስንት ጊዜ ነው...

በብቸኝነት ውስጥ ፣ ለብቻ መቀጣት?

ለካስ አብረሽኝ ነሽ!

ለካስ መሔድ ካለ ፣ ግዴታ ነው መምጣት!!!

37. የሰፋ ሀገር ይዘን ጠቦ መሞት ይብቃን

(ገጣሚ ህሊና ደሳለኝ)

....

...

.

አይችለው የለ እንጂ የልባም ትከሻ፣

ከውርደቱ ደጃፍ ነውሩን ማምለጥ ሲሻ፣

ገርፎ ማሳመን ነው የፈሪ ሰው በትር የሸንታም

ሰው ጋሻ።

እንመን ግድ የለም...

ፍትህ አይታለምም ሀቁን እየሸሹ፣

የጠፋው እንዲገኝ እስኪ መጀመርያ ይፈተሽ

ፈታሹ።

አቀርቅራ ታዝግም ትጎናበስ እንጂ መሄድ

እስኪያድላት፣

ሰብረህ ስታበቃ ምርኩዝ እንኪ ብለህ ደርሰህ

አትደልላት።

በኔ ብቻ በሽታ ጥበት እየቀጣን፣

በእናታችን እርስት በአባታችን መሬት መደገፊያ

እያጣን፣

ቁልቁል እያሰቡ ምንድነው ከፍታ፣

መብት እየነጠቁ ምንድነው ግዴታ?

እስከ መቼ ተረት ግዴለም ይነጋል፣

መንገድ እየቀሙ ምርኩዝ ምን ያደርጋል?

አንተ እንደው ልማድህ አለስልሶ መግደል አሳስቆ

መግፋት፣

ካብኩ እያሉ ማቅለል ሳምኩ እያሉ መትፋት፣

የበደል ላይ ጀግና እሬሳ ላይ መዛት፣

መዋረድን ሸሽት የአሸቃባጭ አፍ መግዛት።

እየሸሹ ትግል እየሮጡ ዛቻ፣

በጉንዳን ልቦና የነብር ዘመቻ።

የበላ እያሰረ የቀማ ቢገፈው፣

የሳተ እያረመ ያጠፋ ቢገርፈው፣

ጀግና ልማዱ ነው ባርያ ሆኖ ታሽቶ ንጉስ ሆኖ

መግዛት፣

እያነሰ ገዝፎ እየሞተ መብዛት።

ያ ሸንታም ላመሉ በሬሳ ይፎክራል፣

ከፈሪ ገዳይ ድል የጀግና ሞት ያምራል።

ይልቅ.....

በእኔ ልቅደም ትርክት የዘር ደዌ አያጥቃን፣

ከጎጥ ቀንበር ፍቱን ጠቦ መሞት በቃን።

የጸደይ ወይን ሆኖ የሀቅ እንባ ቢጥም፣

በድሎ መጀገን ጀብድ ሆኖ ቢረግጥም፣

የትግላችን ልኩ ያሳር ደም ቢያስምጥም፣

በሰፋ ሀገር ጠበን ኢትዮጵያን አንሰጥም!!!

38. "እርጅና"

(አበባው መላኩ)

በንፁህ ልባችን አይሆኑ የሆነው

በለጋው እድሚያችን ስንቱን ያደረግነው

ዛሬ ላይ አርጅተን ሁሉንም ስናየው

ሁሉም ተለውጦ በለሱ በጣለው

የጋለው ቀዝግዞ የፈጠነው ፈዞ

በእድሜ ተገንዞ በእድሜ ተገዝግዞ

ሁሉም ጊዜ ጥሎት ሲያፍ እያየነው

የልጅነት ፍቅር አያረጅም ምነው ??

አያረጅ ምንድን ነው ??

የልጅነት ፍቅር እንደምን ያረጃል እንዴትስ ይጃጃል

ከወለላው ከንፈር ዘመን የሚያሻግር ክትባት ያበጃል

እስከ ገነት ስሞ አለዚያም ተስሞ የፀሀይን ያህል : ትንፋሹ ይፋጃል

እንዲያ እየተፋጀ ፀሀይን ይርቃል

ያለጊዜ መቁነን ብቻውን ይመጥቃል

እርጅናን የት ያውቃል !!

እኔ ልበል እንጂ አረጀው አፈጀው

አሁን ምን ይበጃል አይደለሁ ማረሻ ባለእጅ

ያበጀው

እኔ ልበል እንጂ እሱ በምንት እዳው

ዘመን አይመጥነው ዘመን የማይሸረው

ካንጀቱ ተስሞ ካንጀቱ በሳመው ዘላለም ሚኖረው

በቅንነት ማፍቀር የልጅነት ጥቅሙ ይህው ነው።

ይህው ነው.. ሌላ ምን ወግ አለው.... ሌላ ምን

ወግ አለው ።

የዛሬማ ወጣት በድኩም አካልህ አፍቃሪ ልብ

ይዘህ

በረከሰ ከንፈር ስትሳም .....ስትሳም .....ስትሳም

ደንዝዘህ

ባንድ ሺህ ከንፈሮች እልፍ ዘመን ኖረህ

ከእድሜህ ስትነቃ አካልህ ወጣቱ በወጣትነቱ

ያ " አፍቃሪ ልብህ ውስጥህ ግን ማርጀቱ

እስከ ገነት ሲስም ሲኦልን መክፈቱ

እንኳን ድሮ ሳምን እንኳንም ተሳምን

እንኳን ዛሬ አረጀን ምን በፋራ ቢሆን

ከንፈር እየሳትን ጥርስን እያጋጨን

ያለ ስጋት ወደን ያለ ስጋት ስመን

ብናረጅ አይቆጨን !!!!!!!!!!!!!!!!!!

(⁀ o ‿ ʖ ⁀ o)

39. ሳልነግርሽ...

(በላይ በቀለ ወያ)

.

.

አፍቅሬ እንዳጣሁሽ...

በነብያቶች አፍ፣

ፍልስፍና ሚመስል ፣ ትንቢት ተነገረ

ታምር የሚሰራ...

ጎትቶ ጎትቶ ፣

በመርፌ ቀዳዳ ፣ ግመል አሻገረ

ግመሉ ሲሻገር ፣ መርፌው ተሰበረ።

በሰባራ መርፌ...

ፍቅርሽን ከፍቅሬ ፣ ባንድነት ልሰፋ

ይኸው እደክማለሁ...

ክር ሆነሽ እያጠርሽ ፣ ኖራለሁ ስለፋ።

.....

ሳልነግርሽ...

የኔ አለም ያላንቺ ፣እንደሆነ ራቁት

ባንቺ እንደነበር ፤ ቀንና ሌሊቴ የሚፈራረቁት።

እንደተለየሽኝ ...

አለም ባዶ ሆና ፣ መኖር እንዳስጠላኝ

ፍቅርሽ እከክ ሆኖ...

በልቤ ተተክሎ ፣ ነፍሴን እንደበላኝ።

.....

ሳልነግርሽ...

የነብያት ትንቢት ፣ በኔ መፈፀሙን

‹‹ታምሪያለሽ ›› እያልሁኝ ፣ ‹‹ተአምር ››

ማክተሙን

የተለየሽኝ ለት...

ምፅአት መምጣቱን ፣ የኔ አለም መቆሙን።

.....

ሳልነግርሽ...

ካጣሁሽ በኋላ...

ባለፍኩት ጭንቅ ዓለም ፣ የስቃዬን መአት

አፍቅሮ ማጣት ነው...

በሰባራ መርፌ፣

እውነትን መስፋት ነው ፣ ለካንስ ምፅአት፡

(‾ o ‿ ʖ ‾ o)

40. ሀገር አልባ ባለ ሀገሮች

(በላይ በቀለ ወያ)

.

.

ሁሉም የራሱን ዘር ፣ ከሌሎች ያገዝፋል

ሁሉም የብሔሩን ፣ ክብር ይለፍፋል

ሁሉም ትልቅ ነኝ ሊል ፣ ይኮለታተፋል

እንደ ሀገር የሚያስብ ፣ እንዴት አንድ ይጠፋል?

::::

እንግዳ ተቀባይ

ጨዋ ህዝብ ነን ባይ

ስድብ እያመረተ

ውረፋ ብሸሸቅ ከተበራከተ

እኔነት አብቦ ፣ እኛነት ከሞተ

አፎች ፍቅርን ሰብከው ፣ ልቦች ቂም ከጫኑ

አንድነን የሚሉ ከተበታተኑ

ሰው እየዘነጉ

"ሀገሬን አልረሳም " ፣ እያሉ ቢዘፍኑ

ስላቅ ነው ትርጉሙ

ሮሮ ነው ዜማው ፣ ሾርኔ ነው ግጥሙ።

::::::

ያለፈውን አልፈን

ጨለማውን ገፍፈን ፣ ብርሐን ሳንሰበስብ

ይነጋል እያለ

አንዱ አንዱን ሲጠልፍ ፣ አንዱ አንዱን ሲስብ

አንዱ አንዱን ሲጎትት ፣ ሆነን የአለም ጭራ

እያልን ብንዘፍን ፣ ሀገሬን አደራ

ሹፈት ነው ትርጉሙ

የቀልድ ነው ዜማው ፣ ቅዠት ነው ትርጉሙ

አደራ እየበሉ ፣ አደራን ማቀንቀን

እንዴት ብርሐን እንይ

እኛ እየታወርን ፣ ይነጋል ባልነው ቀን

ለውጥ ኬት ይመጣል

እኛ ሳንለወጥ ፣ ለውጥ ቢናፍቀን?

::::::

እናም እኔ አንዳንዴ

ሲከፋኝ ሲከፋኝ ፣ የማንጎራጉረው

አንድ ዘፈን አለኝ

እንባ ሆኖ የሚያልቅ ፣ በሳቅ ስጀምረው

::::

እናም የኔ ዘፈን

"ሀገሬን አልረሳም

ወገኔን አልረሳም"

በምትሉት ዘፈን ፣ አትፈልጉኝ ነገር

እንዳገር ሳናስብ ፣ ኬፒ አመጣችሁ ሀገር?!

41. "እንደነገርኩሽ ነው"

(በረከት በላይነህ)

አፍሽም ለብቻው - ስሙን እያወጣ

ጆሮሽም ለብቻው - ስሙን እያወጣ

"ወየው ወየው" እንጂ - "ወዬ" የሚል

ሰው ታጣ።

"እግዜሩም እንደ ሰው

ባለመስጠት ሞላ - ከመስጠት ጎደለ

ብጠራው ብጠራው - አቤት አልል አለ"

ማለትሽን ሰምቼ...

እኔ ግን የምልሽ ፤

ምስኪን እግዜርሽን - ከመልክሽ አዛምደሽ -

ከምትጠረጥሪው

እስቲ - ቅፅሉን ተይና - በዋናው ስም ጥሪው።

.

.

ሰሚን ሲበድሉ

ጠሪን ሲበድሉ

ለእግዜርም ቅፅል ስም - አወጡለት አሉ፤

እናልሽ ፦...

በልጥፍጥፍ መአት - ዋናው ገፅ ፈረሰ

ስም አውጪው ሲበዛ - አቤት ባይ አነሰ።

ደሞ...,

አመሌን አመልሽን - ለማያውቁ ሁሉ

ጠርቼው አልመጣም - ትዬኛለሽ አሉ ፤

እሷ የስም ሀብታም - ትጠራው አታጣ - ትሸኘው

አታጣ

እኔ ባለ አንድ ስም - ምን ሰምቼ ልምጣ?

ሰሚን ሲያናንቁ - ጠሪን ሲያቃልሉ

የስም ፋብሪካ ነው - ጉራንጉሩ ሁሉ።

.

.

እንዳልኩሽ ነው ፤

የላክሽው ፎቶ አንሺ - በጥላሽ ከልሎ -

ባንቺ ብርሃን ኩሎ

ፎቶ ነስቶኝ ሄደ - "ፎቶ አነሳሁ" ብሎ።

ፓ! ፓ! ፓ! ካሜራ

ኧረረ!! ካሜራ

በሌሉበት ሁሉ - ማንሳት የማይራራ

ሊያውም በክት ልብስ - ጥለት አዛንቄ

ሊያውም በጀግና ልብስ - በኒሻን ደምቄ

እያገላበጠ - ተዟዟርኩ እያለ - ሲያነሳኝ ሰንብቶ

በትኖልኝ ሄደ - ልብስ የሌለው ፎቶ።

ካሜራሽ ስልጡኑ - ካንቺ እኩል ያወቀ

ፎቶ ያነሳል አሉኝ - ልብስ እያወለቀ።

.

.

እንደነገርኩሽ ነው ፤

የማንም ያልሆነን - ያንተ ነው ተብዬ

በመሠለኝ ፋንታ - ፍሬምሽን ሰቅዬ

ግራ የገባው አይኔ - ከቧልት ይፋጠጣል -

ከእርቃን ይፋጠጣል

የጀግና ፎቶዬ - የበዓል ፎቶዬ - ከሱቅሽ

ይሸጣል።

.

.

አንቺ የመልክ ሀብታም - ቀለም የተረፈሽ

አንቺ የልክ ሀብታም - መስመር የተረፈሽ

የተኩላዎች ክፋት - በበጎች ስም ፅፈሽ

መጥቀሻል ይሉኛል - በምኞት መሠላል

ግድ የለም ምጠቂ ፤

ቅዠት ሲደጋገም - ከህልም ይመሳሰላል።

.

.

እንደነገርኩሽ ነው ፤

ቧልተኛው ዶክተርሽ - በስላቁ ፈዞ

"አከምኩህ" ይለኛል - የራሱን መድሃኒት -

ለህመምተኛው አዞ።

.

.

የህመምተኛሽ ጉዳይ...

የህመምተኛሽ ደሞ - ከዶክተርሽ ባሰ - ሁለቴ

ገደለኝ

"ተመረመርኩልህ ይቺን ዋጣት" አለኝ

"ተ መ ረ መ ር ኩ ል ህ"

በታመመ ልኩ - ጤና ሲሰፍርልኝ

በሽተኛው ልጅሽ - ተመረመረልኝ።

.

.

መድሃኒት ከሰረ - ጤና ተቃወሰ - በሽታ ተስፋፋ

ግብረ ገብ ጎደለ - ስነ ምግባር ጠፋ

ወ ዘ ተ

ወ ዘ ተ...

.

.

ጉባኤ ሰብስበው - ሰበብ ሲያዳምቁ

እኔን የገደለኝ ፣

ከበሽታው ይልቅ - በሽተኛው በውል

አለመታወቁ።

.

.

ያንቺዬማ አይነቱ ፤

ማድማቱን ደብቆ - መድማቱን ለብቻ

እያስመረመረ

ፈውስ በስም ብቻ - ተድበስብሶ ቀረ።

.

.

እናልሽ...

በኔ ና አንቺ አለም ፤

ከማዘን - ማሳዘን

ከመሳት - ማሳሳት

ከደም ማነስ - ደም ማሳነስ

ከመርሳት - ማስረሳት

በእጥፍ ይቀድማል ፤

ከህመሙ በላይ - ህመምተኛው ያማል።

.

.

ኧረ ያንቺስ ነገር

ትንሽ እየሰፋ - ብዙ መቅደድ ያውቃል

ክርሽ ሳይነካ - መርፌሽ ብቻ ያልቃል

.

.

ኧረ ያንቺስ አራጅ - ቅርጫውን ሳንበላው

ያልቅብሻል አሉ - ሞረድና ቢላው።

.

.

እንደነገርኩሽ ነው ፤

ጎዳናው ሳይጠበን - አመል እያጋፋን

እንኳን አካሄዱ - አቋቋሙ ጠፋን።

42. ዝኑፍ ወቀሳ !

(በረከት በላይነህ)

ይለኛል ታዛቢ...

"በእኛ ተረማምዶ - ስኬቱን ሸመተ ፤

ሲመቸው፣ ሲደላው - ትቶን ሰነበተ ! "

ይለኛል ታዛቢ...

"አቅፈን አሳድገን - ከሰው መሐል

ለየን ፤

አለፈለትና - ዞር ብሎም አያየን !"

እኔ ግን እላለሁ !..

"ስህተት የለብኝም ፤

ያለፍኩበት ሁሉ አላሻገረኝም ፤

የረገጥኩት ሁሉ አልተሸከመኝም !"

43. "በእንባሽ ራሰሽ ትፍት"

(በርናባስ ከበደ)

ቀበሌ ሂድና ፥ ድህነት አስመስክር

ይላል አሉ ሃብታም ፥ መፅውቶ ሲሰክር

-

እማኝ ጥራ ይላል ፤ ቀበሌ በተራው

እማኙ ሲመጣ ፤ ይንዛዛል ወረፋው

-

አሹቅ ከጨበጠ ---

ከነዳይ መዳፍ ላይ ፥ ሹም እየዘገነ

"ድሃ!" መባል እንኳን ፥ ገንዘብ ላለው ሆነ።

-------//-------

44. “ጎዳናው”

.

(በረከት በላይነህ)

.

ጎዳናው ይገርማል

ይገርማል መንገዱ

እግረኛው ይገርማል

.

ሸራ ጫማ ባሏይነት በነጫጭ ካልሲ በሲኪኒ ሱሪ

ከመምህሩ ጋራ አይስክሬም ሚልስ ያይስኩል

ተማሪ

ፀባይኛ ወጣት

ጃንቦ ተከልሎ በምርቃና ሆኖ ሐሳብ የሚፈትል

አንዲት ሙ...ደኛ እናት በሏሜ ከልጆቼ አንሳለሁ

የምትል

ፒዛውን የሚገምጥ ጭማቂ የሚመጥ አራዳ

አባወራ

በሚስቱ ትከሻ በልጆቹ ምላስ ቅምጥ የሚጣራ

.

አንድ ፍሬ ሴቶች

.

በተገዛ ቅንድብ በተገዛ ጸጉር በተገዛ ጥፍር

በውሰት ወዘና

የተብለጨለጩ

ማኪያቶውን ከበው ለውስኪ ‘ሚንጫጩ

ጅናም ጅንሳም ወንዶች በሴቶች ጫጫታ

የሚቁለጨለጩ

.

ይገርማል ጎዳናው ይገርማል መንገዱ

ድንቡሸቡሸ ሕፃናት በቶም ኤንድ ጄሪ ሱስ

ቀልባቸው የከሳ

በአይፎኑ አጭልቆ ያንጀሊናን ከንፈር የሚስም

ጎረምሳ

.

ቀውጢ ዳያስፖራ...

.

የሎቲው የቁምጣው የቲሸርቱ ጥለት

የተንዘረፈፈው

አማርኛን ሲሸሽ "what's up" የጠለፈው

.

ነቄ ብላቴና...

.

ከዮፍታዬ ቀዬ ካሆዲስ ዓለማየሁ ከመዝገቡ

መንደር

የአዲስ አፀፃ ጥሪ በቁምጣ ያበረረው

ከቅኔ ተጣልቶ ከግዕዝ ተኳርፎ ሎተሪ 'ሚያዞረው

.

ጸዴ ብላቴና...

.

ከባላገር ዘመን ከጨለማ ዘመን ወደ ብርሃን ጥግ

ተሸጋገርኩ ብሎ

በሸንኮራ ምርኩዝ ከተማ ሚያካልል መቋሚያውን

ጥሎ

ነፍሱ እየሰለለች በከተሜነት ወግ ባሕዶዳነት

ልምሻ

ሲያዘግም የሚውል ሊስትሮውን ጭኖ በታቦት

ትከሻ

.

ፎቆቹ..

.

በመስታወት ቁመት በቆርቆሮ ገጾች ባሕረሙኒየም

ጥራዝ የተብረቀረቁ

የጌቶቻቸውን ዕድሜ ‘ሚያሳብቁ

ሁሉም... ሁሉም... ሁሉም ጥግ ናቸው

ለወደቀ ወገን ይራራል ልባቸው

.

ሁሉም... ሁሉም

ከዘለለት ጥድፊያ ከሰርክ ውጣ ውረድ በተረፈች

አንጀት

ለወደቀ ወገን ምርኩዝ ማበጃጀት

ሁሉም... ሁሉም ይችላሉ

ስለሆዝአር ላለ ይመፀውታሉ

.

.

እኔ ግን... እኔ ግን... ‘ቆጥራለሁ

የሆሜ ክቡር ጀንበር በጎዳና ፅልመት ሲዋጥ

አስተውላለሁ

ጡረታ መንገድ ዳር ሲከፈል ዐያለሁ

‘ቆጥራለሁ... ‘ቆጥራለሁ

‘ቆጥራለሁ አዛውንት በየአቀበቱ በየቁልቁለቱ

ማረፊያ ፍለጋ የሚንከራተቱ

‘ቆጥራለሁ አዛውንት ከልጆቻቸው ፊት

የልመና መዝገብ የገለጡ አሮጊት

‘ቆጥራለሁ በየመንገዱ ዳር

እርጅና ሙሽራው ለምፅዋት ሲዳር

‘ቆጥራለሁ በየሸንተረሩ በየተፋሰሱ

አቀርቅሮ ሲያዘግም እርጅና ሞገሱ

.

.

‘ቆጥራለሁ በሺያደባባዩ

የሸማግሌ ዐይኖች የልጅ ፊት እያዩ

‘ቆጥራለሁ በየሰርጣሰርጡ

በልመና ጉልበት ከሞት ሲፋጠጡ

የሎጅና መዳፎች እሾህ ሲጨብጡ

.

ቆጥሬ... ቆጥሬ... ቆጥሬ

በለማኝ አዛውንት ብዛት ተሳክሬ

የማሰንበቻ ሥንቅ ከኪሴ ቆንጥሬ

ያጽድቆቴን ዋጋ በሳንቲም መንዝሬ

ባዘዘውንት ምርቃት ከሀገር ከቀዬው ትርፌን

ሳመሳስል

በጎዳናው ቀለም ጻድቅ መልኬን ስሥል

ጎልቶ ሚታየኝ ግን የሚያሳፍር ምስል

በቀላል ጥያቄ የነተበ ምስል

.

.

ጥያቄ...

.

.

የዲጄ ኳኳታ የደናሽ ጋጋታ

የድራፍት እርካታ ያሞቄ ድንፋታ

ባጣበበው መንገድ

እንደምን ይቻካል ላሆት ሳንቲም ሰጥቶ በሞካታ

መራመድ?

ለወጣት ሹክሹክታ ለገደል ዝምታ

ላስመሳይ ጫጫታ ላድርባይ እሪታ

በተሰራ መንገድ

እውነት ቀላል ነው ወይ ላሆት ሳንቲም ሰ'ቶ

በሞካታ መራመድ?

ለቡቲክ ሰልፈኛ ለካፌ 'ድምተኛ

ለውስኪ ጭሰኛ ለበርገር ምርኮኛ

በተሰራ መንገድ

እንደምን ይቻላል ላሆት ሳንቲም ሰ'ቶ በሞካታ

መራመድ?

.

.

አያት....አያት...አያትነት ማለት

በደማቅ አሻራ የሸመኑት ጥለት

ለተራኪ ዕድሜ የተሰጠ አንደበት

ባኸት በሞት ጽናት የማይደክም ጉልበት

በልጅ ልጅ መነጽር የማያረጅ ውበት

በልጅ ልጆች ጥበብ የሚታደስ ዕውቀት

የሚታደስ እውነት

አያት ሆኑ ማለት

ድርብ አባትነት

ድርብ እናትነት

.

.

በተለይ እዚህማ... በዚህች ዓይነት ሀገር

ጎጆዋን ላቆመች በተጋድሎ ካስማ ባርበኝነት

ማገር

በዚህች ዓይነት ሀገር

ጥያቄና መልሷን ባዘዘ በቅዳሴ በምትሠራ መንደር

በዱአ በጸሎት በምናኔ ምርኩዝ በከረመች ሰፈር

የአያትነት ዋጋው በልኩ ቢሰፈር

ለሳንቲም ምርቃት ባልተሻማን ነበር!

ታሪክ በመዳፉ ስላደላደለው

ሁሉም ኢትዮጵያዊ ንጉሥ አያት አለው

የልጅ ልጆች ስባት ባያመነምነው

ያያቶቻችን መልክ ሁሌም አንድ ዓይነት ነው

.

እላለሁ... እላለሁ....

የልጆች ምፅዋት ያዘሩቶች ልመና

ያዘሞች ግርግር በሞላው ጎዳና

መንገዱ አይልቅም

ጎዳናው አያልቅም

ይሰፋል ይረዝማል ይሄዳል ይጓዛል

እግረኛው ሞኝ ነው ሳንቲሙን ዘርዝሮ ከወደቁ

አዛውንት ምርቃት ይገዛል

መንገዱ ያስፈራል

መንገዱ ይጨንቃል

ልጆች ሣቅ ሲያንቃቸው አያት እንባ ይጨምቃል

መንገዱ ያሠጋል መንገዱ ያረጃል

ከዘናጭ ልጆች ጎን እርዛት ያዘለ አያት ይወለዳል

ሰጪ ካለቀሰ ተበዳሪ ሥቆ

ጌታ ከለመነ አማኙ 'ግር ወድቆ

ልዑል ከዘመረ ንጉሡ ተዋርዶ

ገጹ ተመሳቅሎ ሸፋኑ ካማረ

ወለሉ ተንቆ ምንጣፍ ከከበረ

ባሸርኛ ስሌት ማነው ያልከሰረ?

.

እላለሁ... እላለሁ

.

ከየጎዳናው ገጽ ጥያቄ አነሣለሁ ጥያቄ እጥላለሁ

እርጅና ለማምሻው ጎዳናን ካመነ

አያት ከልጅ ልጁ ሳንቲም ከለመነ

ባገርኛ ስሌት ማነው ያልመከነ?

በሞዚኦታ ዘመን በምሕላ ዘመን

እመንገድ ዳር ወድቆ ትራፊ መለመን

በጥሞና ዘመን የሚያስቡት ማጣት

በማውረሻ ዕድሜ የሚሰጡት ማጣት

በማልበሻ ዘመን በሸዘት መቀጣት

በለጋሽነት ወቅት በማጉረሻ ዘመን

በጥማት መገረፍ በረኃብ መመንመን

ከሆነ ዕጣችን

ይጠየቅ ትርጉሙ የልጅነታችን

ይፈተሽ መንገዱ የልጅ ልጆቻችን

.

ግድ የለም እንመን

እንመን

.

በሰውኛ ስሌት ውጤቱ ሲሠራ

ትውልድ ያደኸያል ያያቶች ኪሣራ

በልጅ ልጆች ዓለም እንደጉድ ቢደለቅ ቢዘመር

ቢዘፈን

አባት ይወራጫል ባሊያቶች መታፈን

.

አባት ሆይ...

.

ለልጆችህ ርዕዮት ትላንቱን የረሳ ተስፋ ሲደራረት

ሕልሜ ነው ይልሃል ያሊያቶቹ ቅዠት

ከልጅህ አንደበት ቋንቋ እንደዶፍ ቢዘንብ ትርጉም

ቢንፎለፎል ሺ ቃላት

ቢጎርፍም

የልጅ ልጅ አግባቢ ግማሽ ገጽ አይጽፍም

ከልጆችህ ባሕር ዓሣ የሚያጠግቡ ለዓሣ

'ሚስማሙ

ዕፅዋት ተክሎች እንደጉድ ቢራቡ እንደጉድ

ቢያብቡ

ገበታ አይሞላም ተቀዷል መረቡ

.

ግድ የለም እንመን... እንመን

.

የስኬት ክብደቱ የምኞት አይነቱ የነገ ውበቱ ባሻው

ቋት ቢለካ በምንም

ቢሰፈር ባሻው ቃል ቢነገር

ጀግና ልጅ አትወልድም አያቶቿን ገድላ የምትሸልል

ሀገር

.

ከፎቆቹ ጥላ...

.

ከያስፓልቱ ገላ ሲታተም ድምቀቴ

በመስታወት አጀብ ሲጠገን ጉልበቴ

ይኸው አነበብኩት አያቶቼ ፊት ላይ ተጽፏል ሽንፈቴ

በመኪና ብዛት በመስታወት አይነት ሲለካ ፍጥነቴ

በግንብ አጥር መአት በፎቆች ጋጋታ ሲሰላ ስኬቴ

ይኸው ይታየኛል አያቴ ገጽ ላይ ተስሏል ውድቀቴ

ተስሏል ሽንፈት።

45. አማትቦ መባላት

(ረድኤትሺአሰፋ)

.

ከጅቡ ጥርስ ላይ ~በግፍ የተበላቦያንድ ተኩላ

ፀጉር

በንፋስ ተነጥቆ ~ፍትህ እንዲሰጠውቦከፈጣሪው

መንበርቦቆሞ

ሲከራከር !

.

ከተኩላው ጥርስ ላይ ~ሳትዋጥ የቀረች

~የምስኪን በግ ስጋ

እንደ ራሄል እምባቦበፍትህ መቃተትቦየፈጣሪን

ዙፋንቦጩሃ ስታናጋ !

.

ከዛ ከምስኪን በግቦጥርስ ላይ የቀረችቦአንድ

የሳር ዘለላ

በቀል ስትለምነውቦየሰማዩን ጌታቦሰማይ ላይ

በወጣውቦበአቤል ደም

ታዝላ !

.

በዛች ዘለላ ሳርቦዉሃ ተቀምቶቦማዕድን

ተነጥቆቦአመድ የመሰለ

አፈሩ ሲጠቁምቦወደ ሰማይ አምላክቦ" 'ደም '

መልስ " እያለ !

.

በስጋው ብስባሽቦበደሙ አዳብሮቦአፈሩን ያደሰው

የዛ የጅብ ስጋምቦ የዘዉትር ፀሎቱቦ "ፍትሕ !"

ነው የሚለው !

.

"ተወጊ ነኝ! " ባዩቦ መዉጋቱን ዘንግቶቦ ለበቀል

ሲፀልይ

እይዋት ሃገራችንቦ ወደፊትሀለመዉደቅቦ

'ኋላ...ኋላሆ.ስታይ።

46. ..እሳትና ጥበብ...

ሄኖክሸበቀለ

.

ሰዎች እንዲህ ናቸው

.

የትዕዛዝ ዳዴ

ይጎትትህና ~ ስትጀምር መራመድ

እሳት ይሰጡሃል ~ ሸፋፍነው በኣመድ

.

ከሩቅ ይሆኑና...

ከቤትህ ቃጠሎ...

የሚግተለተል ጢስ ~ ይጠባበቃሉ

ግማሹ ተቃጥሎ

ግማሹን ኣተረፍን ~ ኣጠፋነው ሊሉ

.

ብልጥ ከሆንክ ግን

.

ከምላስ ሚወጣ ~ ፍሙንም ተቀበል

ከድርጊት ሚመጣ ~ ግለቱን ተቀበል

ኣመዱን ገላልጠህ ~ ጥበብ ኣክልበት

ሊያቃጥሉህ ሲሹ ~ ኣንተ ብሰልበት

47. «ለአባቴ!»

(በውቀቱ ስዩም)

ሰው ብቻ አይደለህም፣ ካፈር ወጥተህ ላፈር

መላክ ነህ፣ ሉሲፈር

ክብርህ ማንነትህ ባመጽ የሚታፈር፡፤

የማትንበረከክ የማትርመጠመጥ

ከባለጌ ዙፋን በርጩማ የምትመርጥ።

ያለ ባህር ሰርጓጅ ያለ ሙሴ በትር

በመታገስ ብቻ ፣ባህር የምትመትር።

ካዘልከኝ ጀምሮ ፣እንኮኮ ጫንቃህ ላይ

ከፍታውን እንጅ፣ ዝቅታውን ሳላይ

እንደ ንሥር መጠቅሁ፣ እንደ ምስራቅ በራሁ

የገዛ ክንፎቼን፣ እንደ ዳንቴል ሠራሁ።

በርግጥ ደሀ ነበርህ...

ከሰላምታ በቀር የማታበረክት

ነጠላህ መናኛ፣ሰውነትህ የክት

በርግጥ ድሀ ነበርህ

የነጣህ፣ የጠራህ

ከጦርሜዳ ይልቅ ገበያ ሚያስፈራህ።

ቤሳ ባታወርሰኝ አወረስከኝ ትግል

የትም እንዳይጥለኝ ፣ሕይወት እንደ ፈንግል።

አባየ ብርሀን፣ አባ የምስራቅ በር

ገመና ሸሻጊ፣ እንደ ካባ ገበር

አባቴ ባትሆን ይጸጽተኝ ነበር!!!

48. ህገ ሰካራም

(በላይ በቀለ ወያ)

ነገሩ ነው እንጂ ፤ አረቄ አያሰክርም፤

አሳሪ ከሌለ...

ገመድ ሰው አያስርም፤

ወዳጅ ዘመድ እንጂ...

አፈር ሰው አይቀብርም፤

ይላል የሰከረ፤

አረቄ ቤት ሆኖ ፤ መተዳደሪያውን ፤ ህግ እያዋቀረ።

እንደሰካራም ህግ፤ እንደስካር ወሬ፤

አረቄ ቤት ሆኜ..

አረቄ እየጠጣሁ፤ በነገር ሰክሬ፤

ስለ ሰካራም ህግ ፤ ላውራሽማ ፍቅሬ።

እዚህ አረቄ ቤት ከተሰበሰበው የሰደካራም አባል፤

ስሙን የማላውቀው፤ ሰካራም የሚባል፤

አንድ የሰከረ ሰው፤ እንደተናገረው.፤

ሀገርሽ ሀገሬ...

‹‹መልሱን ጠጣንበት›› በሚለው ህግ ነው

የሚተዳደረው።

ለመብራት እያሉን ፤ ገንዘብ እያዋጣን፤

ለመንገድ እያሉን ፤ ገንዘብ እያዋጣን፤

ለውሀ እያሉን ፤ገንዘብ እያዋጣን፤

ለምን መብራት ጠፋ?

ለምን ውሃ የለም?

እንዴት መንገድ አጣን?

ብሎ ከመጠየቅ፤

ሳይሻል አይቀርም...

መልሱን ጠጣንበት፤ የሚል ህግ ማፅደቅ።

ወንጀለኛው ሁላ...

ዳኛውን ጠብቆ ገንዘብ ካቀበለ፤

በ ሺህ ምስክር ፊት...

የመሰረትነው ክስ፤ ውድቅ ከተባለ፤

ለምን እዴት? የሚል...

የከሳሽ ጥያቄ ፤መልስ ካልተሰጠው፤

በሰካራም አንቀፅ...

መልሱን ጠጣንበት፤ የሚለው ህግ ነው፤

የሚረጋገጠው።

እንደ ህገ መንግስት...

ተፈፃሚነቱ፤ ቢሰራም ባይሰራም፤

መልሱን ጠጣንበት ብሎ ያፀደቀው፤ ህግ አለው

ሰካራም።

እንደሰካራም ህግ፤ እንደስካር ወሬ፤

አረቄ ቤት ሆኜ፤አረቄ እየጠጣሁ፤ በነገር ሰክሬ፤

እኔን አረቄ ቤት፤ምን እንደወሰደኝ፤

አረቄ መጠጣት ፤ማን እንዳስለመደኝ፤

አትጠይቂኝ ፍቅሬ።

መልሱን ጠጣሁበት!!

49. ተዓምር

(ሚካኤል ምናሴ)

ጉድ ሆንኩ እኮ አንቺዬ፤

ተዓምራትን ሁሉ ላንቺ ላሳይ ብዬ፤

ወደ ውጭ ወጥቼ ከታች እያየሁዋት፤

አንቺን ደስ እንዲልሽ ጨረቃን ጠራሁዋት፤

አምራና ተውባ ብርሀኗ ለአለም ውበትን ቢሰጥም፤

እውነት እልሻለሁ በማራኪነቷ ከአንቺ አይን

አትበልጥም፤

ጉድ ሆንኩ እኮ አንቺዬ፤

ተዓምራትን ሁሉ ላንቺ ላሳይ ብዬ፤

የጠፈርን ፍጥረት በራሴ መርምሬ፤

ፀሐይን ላመጣት ቀትር ተቃጥሬ፤

በእጄ ከላይ ይዣት እታች ብመለስም፤

እሷም ማቃጠሏ ካነቺ ፍቅር ግለት ግማሹን

አትደርስም፤

ጉድ ሆንኩ እኮ አንቺዬ፤

ተዓምራትን ሁሉ ላንቺ ላሳይ ብዬ፤

ቀናትሽ በሙሉ ደስታ እንዲሆኑልሽ፤

ወፎቹን አስቤ ከቤት ጠራሁዋቸው

እንዲዘምሩልሽ፤

አንቺን ለማስደሰት ቤታችን ቢመጡ፤

የአንቺን ድምፅ ሰምተው ዝማሬውን ትተው

እንደተቀመጡ...ሁሉም ተመሰጡ፤

ጉድ ሆንኩ እኮ አንቺዬ፤

ተዓምራትን ሁሉ ላንቺ ላሳይ ብዬ፤

የሰሜን ተራራን ባንድ እግሬ ወጥቼ ሰውነቴ

ቢያልቅም፤

አንቺን በፍቅር ይዞ የግል እንደማድረግ ልፋት

አይጠይቅም፤

አወየው ተዓምር አወየው ጉድ እኔ፤

ኮከቦች ፍለጋ እንዲያ መባከኔ፤

ብርቅርቅዋን ተዓምር አድርጌ ከጎኔ፤

እናም ይኸውልሽ....፤

በማይሆንሽ ዋጋ በማይመዝን አቅም፤

ተራራ ስወጣ ላንቺ የሚመጥን ተዐምር ስለቅም፤

ዐይኔ ተሸወደ....

ጨረቃን፣ኮከብን ፀሐይን ከሰማይ ወፎችን ከጎጆ

ፍለጋ ቃረመ፤

ልቤ ግን ባለበት ያንቺን ፍቅር ይዞ ተዐምር እየሰራ

ዓለም አስገረመ፤

ካልዳሰስኩ አላምንም

(በእውቀቱ ስዩም)

ሊነጋ ነው ሲሉኝ፤ለኮስኩት ፋኖሴን

ሊወብቅ ነው ሲሉኝ፤ ደረብኩት በርኖሴን

ሰላም ወርዱዋል ሲሉኝ፤ጋሻየን አራገፍኩ

ሰው አልሰማ ብል ነው፤ ክፉ ቀኔን ያለፍኩ፤

ቃል ገብቶ ቃል ማፍረስ

ያገር ልማድ ሁኑዋል፤

እንጀራ እንደ መብላት ፤በበሬ እንደማረስ፤

ፍቅር ስጋ ለበሶ ፤በጁ ካላቀፈኝ

ተስፋም ብብቴ ስር፤ ገብቶ ካልደገፈኝ

ኢምንት ነው ምንም

ካልደዳሰስኩ አላምንም።።

50.የኔነሽ

(ይስማሽ ወርቁ)

የምጠረጥረው፣የማልጠረጥረው፣

ቄሱ መነኮሱ፣ወታደር ደብተራው፣

ያም የኔነሽ ሲላት፣

ያም የኔነሽ ሲላት፣

ለበለበኝ ፍቅር፣አቃጠለኝ ቅናት፣

ወይ ጠንካራ ክንዴ፣ጉልበቴ አያስቀራት!

እንዴት የብቻዬ፣የግሌ ላድርጋት?

ሰው በጠራት ቁጥር፣ባልነቴ ሟሟ፣

የሰማንያ ሚስቴ፣የኔነሽ ነው ስሟ።።

***

51. "አዳሪ"

(አበባው መላኩ)

// //

ሥሚ አንቺዬ!...ይሄን ሁሉ ውበት ይሄን ሁሉ

ሲሳይ

አልፈነው ብንሄድ እንዴት ይቻለናል?

ለይቶ ያማረንን ለይተን ብንወድ ለኛስ ምን

ይለናል?

“ምኔን ነው?” ስላቸው

ውበትሽን ይሉኛል

ሽንጥሽን ዳሌሽን

ደረትና ጡትሽ ይምጣብን ይሉኛል::

ሴትነቴን ወደው

እኔነቴን ንቀው

በፍቅሬ ተማርከው

ገላዬ ሥር ወድቀው

እንደር ይሉኛል በስሜት ታውረው

እነሱ ቀድመውኝ በወንድነት አድረው::

በሴትነት ባድር

ባውንድ እንድቆጥር

ጦም ውዬ እንዳላድር:

አዳሪ ይሉኛል ባስተዳደርኳቸው

ሴትነቴን እንጂ ስሜንና ክብሬን ከቶ ሳልሸጣቸው

ሥሜን ነጠቁና ጠሩኝ በሥማቸው::

የነሱን ሥም ይዤ አዳሪ ተብዬ

ወንደኛ አዳሪዎችን ሳስተዳድር ውዬ

መቼም ሆድ ነውና እንጀራ ነው ብዬ

በሸፍጥ የሰጡኝን ሥሜን ተቀብዬ

በግድ እኖራለሁ አዳሪ ተብዬ::

አለሁበት መጥተው “ወደድን!” ይሉኛል

እኔ ብቀር እንኳ አትቀሪም ብዬ ነው

ሰርክ የለፋሁትን ሰርክ የምገብረው

ምን አስነክተሽኝ በምን ዳብሰሽኝ ነው

ደጀ ሰላምሽን ስስም የምገኘው?

“እኔን ነው?” ብላቸው

እሙዬ ሙች!

ብርሃንሽን ያጥቢያ ኮከብሽን!

“ዓይንሽን!” ይሉኛል

ደረትሽን ዳሌሽን ይምጣብን ይሉኛል::

ደሃ አካሌን ገዝተው

በሴትነቴ ላይ በወንድነት አድረው

በድህነቴ ላይ በሽታ ጨምረው

ከጊዜያዊ ውጥረት ለጊዜው ተንፍሰው

ያው እስካሁን አለሁ ስኖር እንደዋዛ

ሴትነት እየሸጥኩ በሽታን ስገዛ::

ህይወት ጨካኝ ሆና ጨክኜ እምኖረው

ተስፋ ኖሮኝ ሳይሆን ሆድ ስላለብኝ ነው::

ይሄ ነው እንግዲህ ዘወትር የኔ ዕጣ

የበረደው ሲሄድ የጋለው ሲመጣ

የበረደው ሲሄድ የጋለው ሲመጣ...

52. ላ’ንዲት የገጠር ሴት

(በእውቀቱ ሥዩም)

ስትፈጭ የኖረች ሴት፣

መጁ በመጠኗ፣ ወፍጮውም በልኳ ፣

ጓያ ትፈጫለች

ጓያ ሸሮ ሲሆን ያበቃል ታሪኳ።

አስባው አታውቅም..

ወደ ኦናው ምድር ለምን እንደመጣች፣

ከ’ለታት አንድ ቀን፣ከና’ቷ ሆድ ወጣች፣

ከ’ለታት አንድ ቀን፣ ጡት አጎጠጎጠች፣

ከ’ለታት አንድ ቀን፣ ለባሏ ተሰጠች።

ተዚያን ቀን ጀምራ፣

ተዚያን ቀን ጀምሮ፣

ድንግል ድንጋይ ወቅራ፣

ትፈጫለች ሸሮ።

አታውቅም፣

ማን እንደሚባሉ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣

አታውቅም፣

ሹማምንት በ’ሷ ስም፣ ምን እንደሚሠሩ፣

አነሳኹት ‘ንጂ፣ እኔም ለነገሩ፣

በፖለቲካ ጥበብ ራስን ማራቀቅ፣

ምን ይጠቅማትና ጓያዋን ለማድቀቅ።

ከቶ ማንም የለ, አበባ ‘ሚሰጣት፣

ከቶ ማንም የለ፣ ከተማ ‘ሚያወጣት፣

ከቶ ማንም የለ ፣ በዳንኪራ መላ፣ ወገቧን

የሚያቅፋት፣

ልፋቷም፣ዕረፍቷም፣

ወደዚህ መጅ መሳብ

ወደዚያ መጅ መግፋት።

እንደ ዓባይ ፏፏቴ ፣ ሽሕ ዓመት ቢንጣለል፣

ቢጎርፍም ዱቄቱ፣

እንደ ሲኦል ወለል፣ ጫፍ የለውም ቋቱ።

ከዘመናት ባንዱ

መስተዋት ፊት ቆማ፣በተወለወለው፣

ፊቷን ለማዬት፣

ከጸጉራ ላይ ያለው

ዱቄት ይኹን ሽበት. ሲያቅታት መለዬት፣

ያኔ ይገባታል የተሰጣት ዕጣ፣

ከማድቀቅ ቀጥሎ፣መድቀቅ እንዲመጣ።

የመጅ አጋፋፏ-አምሳለ ሲሲፈስ፣

ከቋት ሥስት እንጅ፣ ሢሳይ አይታፈስ፣

ትቢያ ‘ሚተነብይ ዱቄት በዙሪያዋ፣

ከባርኔጣ አይሰፋም፣ የኑሮ ጣሪያዋ፣

‹‹ስትፈጭ የኖረች ሴት ›› ይህ ነው መጠሪያዋ።

53. ያልተማሩ

(መቅደስ ጀምበሩ)

.

የታለ ቅርሳችሁ

የታል ትምህርታችሁ

የለፋችሁበት....የተከላችሁት

ሲያሟችሁ ሰምቼ....

እኒህ ያልተማሩ....

ሀሟበሉ ሲሏቸው.....

ኡሟማለት ጀመሩ

በክብር በማእረግ...

ወርቅ ማጥለቃለቸው

ኡ ለማለት ኖሯል...

ካባ መልበሳቸው ማቅ መደረባቸው

አርሙኝ እናንተ ....እኔ አፈርኩላቸው

ሀ ቢጠፋባቸው

እኔ አዘንኩላቸው።

55. ፈገግታ ነው የሚቀድመኝ

(በእውቀቱ ስዩም)

የድሜ ነፋስ በገላየ : ተረማምዶ ኮበለለ

ልቤን ክንዴን እያዛለ

ያቀፍኩትን እየቀማ : የያዝኩትን እያስጣለ::

እድል በኔ ጨከነ ስል- በምረት እጅ ደባበሰኝ

አንቺ ነጥቆ ከቅፌ ላይ- በትውስታ ደሞ ካሰኝ::

አሰታወሰኝ

አስታወሰኝ::

ወድያው ታይቶ :ጠፊ ኩርፍያሽ

ገራም ሳቅሽ : ልዝብ ልፍያሽ

ያለም ዘፋኝ የማያውቀው

የግልሽ ዳንስ ውዝዋዜ

ትውስ ትውስ ባለኝ ጊዜ

ከግር ጥፍሬ

እስከ ጠጉሬ

ደስታ ነው የሚያቀልመኝ

ያንቺ ነገር ባሰብሁ ቁጥር :ፈገግታ ነው የሚቀድመኝ::

በሰጠሽኝ ፀጋ መጠን: የሰራሽኝ ጉድ አያልቅም::

እኔ ባንች ትዝታ እንጂ: በተራቢ ቀልድ አልስቅም::

ማፍቀር ማለት ለካ ፍቺው : መጃጃል ነው አውቆ ፈቅዶ

ከገደል ላይ መወርወር ነው ተጨፍኖ በራስ ፈርዶ::

አፈቀርኩሽ በየቀኑ :ተጃጃልሁኝ ደጋግሜ

ከገደል ላይ ተከስክሼ: ሞተ ሲሉኝ አገግሜ

ያጥንቶቼን ርጋፊ: እንደዛጎል ለቃቅሜ

እንደ ቆሎ : ጥርሴን ቅሜ

ያደረኩሽ ሲደንቀኝ: ያደረግሺኝ ሲገርመኝ

እፍረት ፀፀት አይደለም: ፈገግታ ነው የሚቀድመኝ !

አውቃለሁኝ ጊዜ ሂዷል :ታሪካችን ተጠቅልሏል::

በሄድንበት ጎዳና ላይ: የመለየት ዝናብ ጥሏል

በርምጃችን ምልክት ላይ: ረጃጅም ሰርዶ በቅሏል

ብቻ ምሾ ቢደረደር: የሆነውን ላይለውጠው

ለንባየማ ፊት አልሰጠው::

ያሳሳምሽ ለዛ ቀርቶ :እንደ እንጎቻ እሚጥመኝ

የነከሽኝ የቧጨርሽኝ: አገርሽቶ ቁስሉ ሲያመኝ

ፈገግታ ነው የሚቀድመኝ!!

56. ካንቺ ጋር

ገጠሚ ገብረክርስቶስ ሟርስታ

,

ካንቺ ጋር ሁሉም ነገር ሄዷል

ሰዓቱ ተረስቷል ቀኑም ሌላ ሆኗል

ዓመተ ምህረቱ

በጋና ጸሀዩ

የኖርሽበት ቤቱ

አልጋ ጠረጴዛው ስጋጃ ወንበሩ

መስኮቱና በሩ

ስዕሉ ግርግዳው

ካንቺ ጋራ ጠፍቷል

ሁሉም ተለውጠው

ዛሬ ነገ የለም

ቅናትና ፍቅሩ ሀዘኑ ጨዋታው

ደስታና መከራው

ፈጥሯል ሌላ ቀለም

ገርጥቶ ጠውልጎ መልኩ የነበዘ

ሞቷል መታሰቢያሽ ሆኗል የፈዘዘ

ፈራርሷል የካብሽው

ትዝታው የድሮው

ቀርተሽ ተረስተሻል

ጠፍተሻል ከልቤ

ወጥተሻል ከቤቴ

ወጥተሻል ካንጀቴ

ወጥተሻል ካጥንቴ

ሄደሻል ካሳቤ።

የለሽም የለሽም

ሙዚቃ ድምጽሽን

እንደ ዱሮ አልሰማም

ቅዠት ዘፈንሽ ዜማሽ እንጉርጉሮሽ

ጭጋግ ነው ውበትሽ

የጊዜው መለወጥ

ገላሽን ደብቆ ጋርዶታል መልክሽን

ጥላሽ ነው የቀረው አካልሽ ተሰርቶ

ጨብጦ ቅርጽሽን

ሳቅና ፈገግታሽ ጨዋታና ቀልድሽ

ለዛና ወሬሽ

ቅንድብሽ ሽፋልሽ

የሚያበሩ አይኖችሽ

ጣፋጩ ከንፈርሽ

ለስላሳው ምላስሽ

በረዶ ጥርሶችሽ

ተለውጠው የሉም

ካሳቤ ጨለማ ገብተው አይታዩም

ያ ውብ ቆንጆ ባትሽ

የሚዋጋው ጡትሽ

የሚቆጣው ዳሌሽ

ካንቺ ጋር ሄዷል።

57. የማታሸጀምበር

(ሰዓሊና ገጣሚ ገብረክርስቶስሸዊስታ)

ካንዱ ቤት ወዳንዱ

በጣራው ተራምዳ፣

የጋራውን አናት እየነካች ሄዳ፣

እዩት ከስር ጥላው፥

የማይደርስበትን፣

እዩት ሰው ጥላው፥

ሲለፋ ሲባክን።

58. ሰው ሲሸነፍ

ገብረክርስቶስ ሟስታ

.

.

ማሸነፍ ምንድን ነው?

የምኞት አዝመራ፣ የደስታ መከራ

የታጨደ ጣጣ፣ የታወቀ ችግር

የሞት መከራ፣

የሚነድ እሳት ነው ተዳፍኖ የበራ።

እያደር ጠፊ ነው::

እያደር ቀሪ ነው ሲቆይ ይሰለቻል

ዋጋው ይቀንሳል::

.....በመሸነፍም ነው

ሰው ደስታ ያለው::

በመተው፣ በመርሳት

በመልቀቅ በማጣት

በመሸሽ በመፍራት::

ወደፊት ከመሄድ አውቆ በማፈግፈግ

ከማሰብ ለብዙ ጥቂት በመፈለግ

በማነስ ከማደግ::

በመጣል ከማንሳት፣ በመስጠት ከመውሰድ

በማልቀስ ከመሳቅ፣ በመቅረት ከመሄድ

ከመውጣት በመውረድ::

ከመልበስ መታረዝ

ከማምለጥ በመያዝ

ክብርን ለመጠበቅ ደፍሮ ከመናገር

አንገት በማቀርቀር

በመዋረድና በችግር ተጎድቶ

በመውደቅ ተገፍቶ፣ በመናቅ ተጠልቶ

በጎዘን፣ በድካም፣ በሕመም ባርምሞ

አግኝቶ በመስከር በመሻር ተሹሞ

ያውቃል ማ መሆኑን

ይረዳል አቅሙን::

የሕይወት ለውጥ ነው ያለ በኑሮ ላይ

እንደ ቀን ፣ እንደ ሌት፣ እንደ መሬት ሰማይ

እንደ ውሀ እንደ ሳት እንደልቅሶ ሳቅ

እንደርጥብ ደረቅ

ሁሉም ተለውጦ አንፃሩን ይይዛል

የሚሮጠው ጊዜ ጥቂት ይታገሳል::

ሰዓቱ ይቆማል

ደቂቃው ይተኛል::

ይሸፈናል ወሩ

ይታሠራል ቀኑ

ቀስ ይላል ዘመኑ::

የሚፈጥነው ሐሳብ ከጉዞው ሲመለስ

ያንዣብባል መንፈስ

የምትራወጠው ትቀመጣለች ነፍስ::

አጥንት እና ጡንቻ

ጅማትና ሥጋ

ዝለው ይወድቃሉ

ሰላም ያገኛሉ::

ዕረፍትና ድካም ያሳዩታል ቤቱን

ይተኛል ዕንቅልፉን

ሲያውቀው መሸነፉን::

---

59. ‹‹አልነጋም››

(ገጣሚ በላይ በቀለ ወያ)

ፀሐይ ስትወጣ- ‹‹ነግቷል›› ለምትሉ

ንጋት ላልገባችሁ- ጨለማዎች ሁሉ

አልነጋም ነው መልሴ- ለናንተ አኩኩሉ፡፡

አልነጋም

አልነጋም

አልነጋም

አልነጋም

እንደኔ ላለ ሰው

በረሀ ተወልዶ-በረሀ ላደገ

ፀሐዩ ጠላቱ ነች

ሰርክ የሚደበቃት- ጥላ እየፈለገ፡፡

60.

(በላይ በቀለ ወያ)

.

.

ሰው ሀገር ሆናችሁ

ሞቴን ባገሬ አርገው ፣

ምናምን ብላችሁ ፣ አታውሩልኝ ወሬ

ሬሳ ሰብሳቢ..

ጥንባንሳ አይደለችም ፣ ኢትዮጵያ ሀገሬ።

::

ህይወታቹ እንጂ

እውቀታችሁ እንጂ ፣ የሚበጀው ላገር

ሞትማ ያው ሞት ነው!

የትም ቀባሪ አለ ፣ የትም አለ አፈር።

61. ቀን አልባ ቀናቶች

(በላይ በቀለ ወያ)

.

.

ያልወለዱ እናቶች

ያላጠቡ ጡቶች

በወላድ አንደበት ፣ ሳይመሰገኑ

ቀን አልባ ቀናቶች

አመትን ተሻግረው ፣ ዘመንን ሳይደፍኑ

ቀን ሳለ እንገናኝ ፣ ቀን ሳለ እንወያይ

ወይም "ዋ" እንበል ፣ ወይም ደግሞ "ዋይ ዋይ"

ወይም አንድ እንሁን ፣ ካልሆነ እንለያይ።

::::::::::

ወላድ በማጥባቷ

ደረቷን ሳትደቃ ፣ ጡቷን ሳትረግም

ሀዘን ልኩን አልፎ ፣

እንባ አላግት ብሎ ፣ ዐይናችን ሳይለግም

ቀን ሳለ እንገናኝ

ቀን ሳለ እንተያይ ፣ ቀን ሳለ እንግባባ

ቀን በሌለው ቀን ውስጥ

እዬዬም ድሎት ነው ፣ የምቾት ነው እንባ።

::::::

62. ማህሌተ ገንቦ

(በእውቀቱ ስዩም)

.

.

"ባጭር ቀረን" ስንል ፣ እድሜ ላበደሩን

ቀርፀው ላሳመሩን

ለኩሰው ላበሩን

ቺርስ!!

::::::

ፊታችንን ዐይተው

እንደተቸገር-ን ፣ ካይናችን ላወቁ

"ስለማርያም" ብለን

እስክንለምናቸው ፣ ቆመው ላልጠበቁ

ቺርስ!!!

::::::

ወድቀው ለማይጥሉ ፣ነግሰው ለሚያነግሱ

ነውራችንን ዐይተው

ልክ እንደ ድመት ኩስ ፣ ለሚያለባብሱ

ብድር አበድረው ፣ ፈጥነው ለሚረሱ

ቺርስ!!!!

::::፣

ላባ ላረጉልን ፣ የመከራ ሸክሙን

ቀልደው ላሳቁን ፣ተጫውተው ላከሙን

በቸከ ዘመን ላይ

ስጋ ለበስ ትንግርት ፣ ሆነው ላስደመሙን

ቺርስ!!!!!

63. መንታ ነው ፍጥረትሽ

(1968 ደበበ ሰይፉ ለያብርሃን ፍቅርሏ)

.

ተገለጠ ዕቶኑ ተከፈቱ ዓይኖችሽ

ብርሃን አዘነቡ፤

ቀለማት አቅርረው ውበትን አነቡ፣

ጋረዱት ኮከቤን ብርሃን አጠሉበት

ኩራዜን በማሾ አደናገዙበት።

ክንዶችሽ አቀፉኝ አቅፈው አባበሉኝ

አባብለው አስተኙኝ

ውጋቴን ነጥቀውኝ ቁስሌን አዘናጉኝ

ከሰመመን ጀርባ እሾህ ላይ ሊያነቁኝ

ቁርንጮ ሊያለብሱኝ በማቅ ሊፈትጉኝ።

ሰጠሽኝ ጨለጥኩት የፍቅርሽን ጽዋ

ባንድ የተቀመመን ማር እና ግራዋ።

ምን ይሆን ፍጥረትሽ ጥንድ የሆነ መንታ

ከቃልሽ ያልጠፋ ብስራት እና መርዶ

ዋይታን እልልታ።

ያልቃሾች ሙሾ ነሽ የዕድምተኞች ጨዋታ

የሐሴት ርችት የሐዘን እሩምታ።

64. የዓለም መራራነት

ገጣሚ፡- ገብረ ክርስቶስ ደስታ

(መንገድ ስጡኝ ሰፊ፣ ገጽ 62)

.

ያለም መራራነት ነው የሚጣፍጠን

መቸ መጣፈጧ፤

ኮሶውን በማሯ ጠቅልላ ስትሰጠን

ስትሰጠን እሳቱን

አመድ አስመስላ ሸፍና ረመጡን።

ስትሰጥ ማየ ሕይወት ስትሰጠን መድኃኒት

መርዟ ጨምራበት።

ስትሰጠን እሬቱን ስኳር አስመስላ

እንደጎመን ሠርታ ሳማዋን ስንበላ፡

እሷ ትዞራለች

ፀሐይ ትሞቃለች

እኛን በብርድ ላይ በጨለማ ጥላ።

ያለም መራራነት

የሚያቆራምድ ነው፤ የሚያኮራምት።

ስትወስድ ወደኋላ ስትወስድ ወደ ሌላ

ምሥጢር ያላት መስላ።

ከቤተሰብ ማሕል

ሰው ስታስኮበልል።

ስትወስድ ስጦታዋን

ለገጸበረከት ያቀረበችውን።

ሌባ ናት ሰራቂ

ቀጣፊ ነጣቂ።

አቀባባይ ቀልማዳ፤ አታላይ አስመሳይ

ዋሾ ናት ወላዋይ።

ሰው ሊኖር ባለም ላይ መች ተፈጠረ!

መንገደኛ እንግዳ

መሸቶበት የመጣ

ሠራተኛ አገልጋይ ነው የተቸገረ።

ብዙ ነው ልፋቱ

ሲፈጠር፤ ሲመጣ፤ ሲወጣ ከቤቱ።

አይችልም መዝናናት

በደመነፍስ ባሕርይ እንደተቀረጹት።

እንዳህያ እንደጅብ ወይም እንደጦጣ

ወይም እንዳንበጣ

የማይቸገሩት ለምን ያስባሉ?

ከብቶች ይግጣሉ፤ ወፎች ይዘፍናሉ

አበቦች ያድጋሉ።

ውስጡን አላወቁም፤ አልተመራመሩም

ሲመጡ ወዳለም።

የውሸት ሥዕል ናት

ለዛዋ እሚጠፋ ቀለሟ እሚጠፋ።

ጠረኗ እሚያባርር፤ ጣሟ እሚከረክር

ቧልቷ የሚያስመርር።

የሰው ልጅ አንድ ባንድ ልታንሸራሸረው

ሁልጊዜ እንግዳ ነው

ማናፈስ ማቅበጧ

ማቻኮል ማሮጧ።

ያለም መራራነት ነው የሚጣፍጠን

መቸ መጣፈጧ!

65.

ትርጉም !

(በረከት በላይነህ)

..

"አስቀያሚ፣

አሰጠሊታ ፣

መልከ ጥፉ፤

እንደ ደሀ ቀዬ መስቦችህ የረገፉ!

የማትባል እዚህ ግባ ፣

የሰው ፍራሽ ፣ ማማር አልባ!

ፊተ መአት ፣ ያመድ ክምር!

የጭራቅ ሳቅ ያይጥ˙ ድምር

ባትታይም የማታምር! !!"

እረ ! ሌላም፣ ሌላም፣

ትልሀለች ብለው የነገሩኝ ለታ ፤

አቤት ሀሴት ፣ አቤት ደስታ!

ለምን ብትይ?

መልኬ ከሸለመሽ የማይሸር ጥላቻ ፤

ደስታ አሰከረኝ 'ስላየሺኝሀጣቻ

66. አስደግማብኝ ነው...

(ሰለሞን ሳህለ)

.

ለሰባት ጠንቋይ ልጅ ለደብተራ ምርኩዝ

ጠጠር ገበጣ አርጋ ላኬር እጣው እርኩዝ

ይቺን ያየ አስብላ

መሬት ልታስገባ ድቼ ልታስበላ

የስር ማሽ እንጉዳይ የኮከብ ቆጣሪ

የነ መገን ቦቃ የነ ጥና ጠሪ

ያንደርቢ ቁጣ የአመድ ላይ ዘዋሪ

ለመቃብር አፈር መንገድ ላይ ቀጣሪ

መተተኛ ፍቅር ልብ ላይ ቀባሪ

የቀን ስደተኛ አርጋኝ የሌት ዟሪ

አቅሌን እያሳተች ምታስብለኝ እሪ

አስደግማብኝ ነው...

በርሶ መጀን ብላ

የልቤ ሳይበቃት ልቦናየን በልታ

ጨፌ እየነከሰች በጉልበት ተደፍታ

ኩራቴን ልትነጥቀኝ ኮርታ ልትማታ

ተማትታም ልትረታ

ጥላየን ጀማው ፊት መሬቱ ላይ ዘርታ

ያዙልኝ እያለች በጠንቋይ ቱፍታ

መለመላ ነፍሴን ወናየን ዘርግታ

አፍሮ ይኑር ብላ እኔን አስወግታ

እርጋታየን ነጥቃ እኔን ከኔ አጣልታ

በደብተራው ምርኩዝ ባስነካችው ኩታ

እንዳነክስላት ጅስሜን አስመትታ

ህልሜን እንዳልሰማ ልቤን አስመትታ

አስደግማብኝ ነው ናልኝ ብላ ጠርታ

የሆንኩ አንገት ደፊ የሆንኩት ከርታታ

መለየት ያቃተኝ ቀኑንና ማታ

አስደግማብኝ ነው...

አስደግማብኝ ነው...

ለነ ጥላ ወጊ ለመጫኛ ነካሽ

ለነ አፍዝ አደንግዝ ለዱር ቅጠል በጣሽ

ለመንገድ ገርጋሪ ለውቃቢ ዘራሽ

ለገሃድ ስውሩ ለነ ጽናት አፍራሽ

ለምድር ላየሩ ለየሎስ አጎንባሽ

ለባህር ለየብሱ ለጠቋሪት ደጋሽ

አስደግማብኝ ነው

ወለም ያላለኝን ዘላለም የምታሽ

አስደግማብኝ ነው...

67. ፍጥነት እና ነፃነት !

(በላይ በቀለ ወያ)

.....

አልጋ ባልጋ ሆኖ

የጥንቸሎች ፍጥነት ፣ ፍጥነት ከተባለ

በኤሊዎች ጫንቃ

እራሱን ያልቻለ ፣ ግዙፍ ድንጋይ አለ።

ያንን ግዙፍ ድንጋይ

ከኤሊ ጫንቃ ላይ ፣ ላፍታ ቢነሳላት

ከጥንቸሎች ፍጥነት

አስር እጅ የሚሻል ፣ በቂ ፍጥነት አላት።

ያንን ግዙፍ ድንጋይ

ለዘመናት ቀርቶ

ለሰዓታት ያህል ፣ ጥንቸል ብትሸከም

መሮጡ ይቅርና

መራመድ አትችልም ፣ ነፃ ባልሆነ ዓለም።

ፍትህ በጎደለው ፣ ነፃ ባልሆነ ሀገር

ድንጋይ ተሸክሞ

የፈጠነ የለም ፣ ከኤሊ በስተቀር!!

ፍትህ በሞላበት ፣ ነፃ በሆነ ሀገር

ይቻላል ቀላል ነው ፣ ክንፍ አውጥቶ

መብረር!!!!!!!!

68. ሀገሬ

(ሰአሊና ገጣሚ ገብረ ክርስቶስ ደስታ)

አገሬ ውበት ነው፣

ለምለምና ነፋስ የሚጫወትበት፣

ፀሃይ የሞላበት፣ ቀለም የሞላበት።

አገሬ ቆላ ነው፣ ደጋ ወይና ደጋ፣

እዚያ ብርሃን አለ ሌሊቱ እስኪነጋ።

አገሬ ተራራ ሸለቆ ረባዳ፣

አገሬ ጅረት ነው ገደልና ሜዳ፣

ውበት ነው በበጋ ፀሃይ አትፋጅም፣

ክረምቱም አይበርድም፣

አይበርድም፣ አይበርድም።

አገሬ ጫካ ነው፣

እንሰሳት አራዊት የሚፈነጩበት፣

በወጥመድ ሳይገቡ ሳይነካቸው ጠላት።

እዚያ አለ ነፃነት፣

በሃገር መመካት፣

በተወላጅነት፣

በባለቤትነት፣

እዚያ አለ ነፃነት።

አገሬ ሃብት ነው፤

ጎመኑ ስብ ጮማ፣ ቆሎ ክትፎ ስጋ፣

ድርቆሹ ፍትፍት ነው፣ ቃሪያው ሙክት ሠንጋ፣

ጠጁ ነው ወለላ፣

ከኮኛክ ያስንቃል የመንደሩ ጠላ።

እህሉ ጣእም አለው እንጀራው ያጠግባል፣

ከቢራ ከሻምፓኝ ውሃው ይጣፍጣል፣

በዓሉ ይደምቃል፣

ሙዚቃው ያረካል፣

ጭፈራው ዘፈኑ ችግርን ያስረሳል።

እዚያ ዘመድ አለ፣

ሁሉም የናት ልጅ ነው፣

ሁሉም ያባት ልጅ ነው፣

ጠላትም አንዳንዴ ይመጣል መቃብር፣

ባለጋራም ቸር ነው “ያገር ልጅ ሲቸገር” ፤

ገነት ነው አገሬ።

ምነው ምን ሲደረግ ?

ምነው ለምን እንዴት ?

ዘራፊ ቀማኛ ምቀኛ ወንበዴ፣

ጥርኝ አፈር በጁ ስንዝር ወሰን አልፎ፣

የተቀደሰውን ያፍሪቃ ላይ ደሴት፣

ባያገኝ ለማርከስ ጠላት ይመኝ እንዴት።

እምቢኝ አሻፈረኝ፣

አሻፈረኝ እምቢ፣

መቅደስ ነው አገሬ፣

አድባር ነው አገሬ፣

እናትና አባት ድኸው ያደጉበት፣

ካያት ከቅደም አያት የተረካከቡት፣

አፈር የፈጩበት፣

ጥርስ የነቀሉበት።

አገሬ ዓርማ ነው፣ የነጻነት ዋንጫ፣

በቀይ የተጌጠ ባረንጓዴ ቢጫ።

እሾህ ነው አገሬ፣

በጀግናው ልጅ አጥንት የተከሰከሰ፣

ጠላት ያሳፈረ አጥቂን የመለሰ።

አገሬ ታቦት ነው ፣ መቅደስ የሃይማኖት፣

ዘመን የፈተነው በጠበል በጸሎት።

ለምለም ነው አገሬ፣

ውበት ነው አገሬ፣

ብሞት እሄዳለሁ ከመሬት ብገባ፣

እዚያ ነው አፈሩ፣ የማማ ያባባ።

ስሳብ እሔዳለሁ ቢሰበርም እግሬ፣

አለብኝ ቀጠሮ ከትውልድ አገሬ።

አለብኝ ቀጠሮ

ከትውልድ አገሬ፣

ካሳደገኝ ጓሮ።

69. ሙግት

((በውቀቱ ስዩም))

ጊዜ ለሰው ህይወት

ዘበት አይታክተው

እኔም ምላሽ ባጣም

መጠየቄን አልተው።

ኩታ ገጠም ናቸው

አልፋና ኦሜጋ

እንዴት ቀን ይመሻል

በቅጡ ሳይነጋ?

ማን ዘረፈው ጠጉሬን?

ማን አሰረው እግሬን?

ጉልበቴን ምን በላው?

አቅሜን ማን ወረሰው?

ተወልዶ ሳይጨርስ

እንዴት ያረጃል ሰው?

70. "ፍርሃት እና ናፍቆት"

© ዶሟር ፈቃደ አዘዘ

ይመጣል እያሉኝ፣የደስታ ጊዜ፣የሰላም

ዘመን

የት ደርሷል ስላቸው

ይኸው ድርሷል ሲሉኝ

ናፍቆቱ፣ናፍቆቱ፣ናፍቆቱ ገደለኝ

ይመጣል እያሉኝ አስቸጋሪ ጊዜ የከፋ

ዘመን

የት ድርሷል ስላቸው

ይኸው ደርሷል ሲሉኝ

ሥጋቱ፣ሥጋቱ፣ሥጋቱ ገደለኝ

71. ቢታነፅ ቢወቀር

(በእውቀቱ ስዩም)

.

እኔም አንድሰሞን

ልክ እንደሶሎሞን

"ሁሉም ከንቱ ከንቱ ነፋስን መከተል"

ላይጥሉ መታገል: ላይከብሩ መባተል

እያልሁ አጨልሜ

በራሴ ለግሜ

እፈላሰፍ ነበር::

ከዚያ አንቺን አገኘሁ

በጉዋሮ በር በኩል: ሰሎሞኔን ሸኘሁ

መፈጠሬን ወደድሁ

ነፋስ አሳድጄ እንደቆቅ አጠመድሁ::

ከፀሓይዋ በታች :ግልገል ፀሃይ ፈጠርሁ

ለኦናው አምፖሌ: ብርሃን አበደርሁ

ማቅ የነበረው ጨርቅ: ሸማ ሆኖ ቆየኝ

"ከንቱ "የነበረው "አንቱ "ሆኖ ታየኝ::

ለካስ

ጠቢብ ቢያስተምረው

መከራ ቢመክረው

አካሉና ልቡ : ቢታነፅ ቢወቀር

ሰው አቅሙን አያውቅም : ካልወደደ በቀር::

72. መልክአ እናት

በዕውቀቱ ስዩም፣ የግጥም ስብስብ፣ 2001

ዓ.ም

ሰላም ለኪ እናታችን

ባለሸበት እንዳለሸ

አንቺ የተባረክሽ ነሽ

ሰላም ለዓይኖችሽ

ከጭስ ጋራ ለሚሟገቱ

ከእንቅልፍ ጋር ለተፋቱ

ተቅበዝባዥ ፍጡር ሆኜ ኑሮዬን ከምገፋ

ምነው እንባሽን በሆንኩ

ከዓይኖችሽ ስር እንዳልጠፋ።

ሰላም ለከንፈሮችሽ ትላንት ለማውቃቸው

ዛሬ ለምናፍቃቸው

ውዳሴ ክብር ምርቃት

ጭብጨባ ሙገሳ ሽልማት በተረፈበት ቀዬ

ምነው ያሞቺን እርግማን - ይናፍቃል ጆሮዬ

ከሌሎች ውዳሴና ክብር እልፍ ጊዜ የተሻለ

ለካ በሎግማንሽ ውስጥ እናትነትሽ አለ።

ሰላም ለጣቶችሽ

ለሰዎች የቀረቡ፣ ከራስሽ ግን የራቁ

መስጠት መለገስ እንጂ መቀበልን ለማያውቁ

ሰላም ለኪ!

ባለሽበት እንዳለሽ።

---

73. የማጋራት ጣዕም

(በረከት በላይነህ የመንፈስ ከፍታ፣ ገፅ 66)

.

ብልህ!

ስንጥቅ ምጣድ ጣደ ፣

ሽንቁር ድስቱን ጣደ ፤

ቅጠሉን ፣

እንጨቱን ፣

ኩበት ...ምናምኑን በእርጥቡ ማገደ ።

እንክርዳዱን ፈጨ ፣ ያለእርሾ አቦካ ፤

የነቀዘ ጓያ በሽሮ ስም ከካ ።

ዲቃላውን ድንች ፣

ከደረቀው ሽንኩርት ፣

ከወየበው ጎመን ፣

ከሸክላው በርበሬ - ያለጨው ቀየጠው ፤

ከዚያ !

"እንብላ !" ይለናል 'በሰውሆኪያጣፍጠው

74. ልብና መስታወት

(በረከት በላይነህ)

(የመንፈስ ከፍታ፣ ገፅ 29)

.

አንዳችም ሳይጨምር፣ አንዳችም ሳይቀንስ፣

በተሰጠው መጠን ለሁሉም ሲመልስ፣

ከትዝታ ገጹ ምንም ሳይጽፍበት፣

መስታወት ብቻ ነው ኑሮን ያወቀበት።

ልብ ግን አቃተው!

በመጣው ሲደሰት፣ በሄደው ሲከፋ፣ውለታ

ሲደምር፣ ቅያሜ ሲያጠፋ፣

ከሚስጥር ሆድ ዕቃው ነገር ሲያመሰኳ፣

ቀለም አልባ ሆነ-ይቅርታችን መልኳ።

75. ሀገር ማለት የኔ ልጅ

(ዶሟር በድሉ ዋቅጅራ)

.

ሀገር ማለት ልጄ፣ ሀገር ማለት፣

..

እንዳይመስልሽ የተወለድሽበት ቦታ ፣የተወለድሽበት አፈር፤

እትብትሽ የተቀበረበት ፣ ቀድመሽ የተነፈሽው

አየር፤

ብቻ እንዳይመስልሽ።

ሀገር ረቂቅ ነው ቃሉ

አገር ውስብስብ ነው ውሉ

.

ሀገር ማለት ልጄ ፣

ሀገር ማለት ምስል ነው ፣በህሊና የምታኖሪው፤

ከሠማማ ማህጸን ከወጣሽበት ቀን ጀምሮ ፤

በጠባሽው ጡት፣ ወይም ጡጦ ፣

በዳህሽበት ደጃፍ፣ በወደቅሽበት ፈፋ፤

በተማርሽበት ትምህርት ቤት፣

በተሻገርሽው ዥረት ፤

በተሳልሽበት ታቦት ፣ወይ በተማፀንሽው ከራማ ፤

በእውቀትሽና በህይወትሽ፣

በእውነትሽና በስሜትሽ ፣

የምትቀበይው ምስል ነው ፣ በህሊናሽ የምታኖሪው፤

ስትወጅ ሰንደቅ ታደርጊው

ቢያስጠላሽ የማትቀይሪው

ሀገር ማለት የኔ ልጅ ፣

ሀገር ማለት ቋንቋ ነው በአንደበት አይናገሩት፤

በጆሮ አያዳምጡት፤

አማርኛ ኦሮሞኛ ፣ አፋርኛ ቅማንተኛ፤

ጉራግኛ ወይ ትግርኛ፣ ብለው የማይፈርጁት

.

የኔ ልጅ፣

አማራውና አፋሩ፣ ኦሮሞው ሲዳማው ፣ጉራጌኛሽን ባይሰማ፤

ያልገባው እንዳይመስልሽ ፣ ሀዘን ደስታሽን

ያልተጋራ

የየልቦናችንን ሀቅ፣ ፍንትው አድርጎ እያሳየ፤

ህዝቦችን ከሰንደቃቸው፣ አስተሳስሮ ያቆየ።

ሀገር ቋንቋ ነው ልጄ፣ የሁለንተናሽ መስታወት፤

ሲከፋሽ ትሸሸጊበት ፣ ሲደላሽ ትኳኳየዪበት

.

የኔ ልጅ ፣

አያት ቅድም አያትሽ ፣ሰላም ሲሆን ከወልቂጤ

አድማስ ማዶ ሸቅጦ፣ሲያቀና ወረቱን፤

ለእኔና ለአንቺ መኖሪያ፣ ሲያቀና ቀዬና ቤቱን፤

ሀገር ጠላት ሲደፍራትም፣ ጦሩን ሰብቆ እየፎከረ፤

ከኦሮሞው ከትግሬው፣ ከአፋሩ ከወላይታው፣ . . .

ከሁሉም የጦቢያ ልጆች ፣ አጥንቱን እየማገረ፤

ሀገር ይሉት መግባቢያ ፣ሰንደቅ ይሉት መለያ ፣

ሲያቆይልሽ፤

በጉራግኛ ማትገልጭው፣ በጎጥ የማትገድቢው፣

ስንት አለ ታሪክ መሰለሽ!

እና የእኔ ልጅ፣

ለዚህ ነው ሀገር ይሉት ቋንቋ፣ ላንቺ የሚያስፈልግሽ፤

ከወልቂጤ አድማስ ማዶ፣ ለተሳሰረ ታሪክሽ፤

ከወልቂጤ አድማስ ማዶ ፣ ለተወጠነው እድገትሽ

እና ልብ በይ ልጄ ! ሀገር ማለት ቋንቋ ነው፣

ባንደበት አይናገሩት፤

በጆሮ አያዳምጡት

.

ከሁሉም በላይ ልጄ ፣

ተፈጥሮ ከቸረው በረከት ፣ የላቡን ፍሬ የሚበላ፤

ሀገር ማለት ወገን ነው፣ የእኔ የምትይው ከለላ

ትመኪበት ጥሪት፣ ትደምቂበት ብርሃንሽ፤

የሰብዕናሽ ግማሽ ውል ፣ወገን ነው ማሕተምሽ።

ዜጋው ነው ልጄ ሀገርሽ።

መሬትማ የእኔ ልጅ፣

በእምነትሽና እውቀትሽ፣ ከልለሽ ካላበጀሽው፤

ለእድገትሽ ውጥን ካልሆነ ፣ለተስፋሽ ካልተመገብሽው፤

መሬትማ ባዳ ነው፣ ላለማው የሚለማ፤

ለተስማማው የሚስማማ

ዥረቱም ግድ የለውም ፣ ቦይ ለማሰለት ይፈሳል

ተራራውም ደንቆሮ ነው ፣ ለቦረቦረው ይበሳል።

መሬቱ አደለም የኔ ልጅ፣ እድርተኛው ነው ሃገርሽ፤

ስትቸገሪ ታድጎ፣ ስትታመሚ አስታሞ፣ ስትሞቺ አፈር ሚያለብስሽ።

በእጅሽ ያለ ብሩህ ጽጌ ፣ ሰው ነው ልጄ ሀገርሽ፤

ወገን ነው ልጄ ሀገርሽ።

እና የኔ ልጅ፣

ሀገር ረቂቅ ነው ቃሉ፤

ሀገር ውስብስብ ነው ውሉ

76. በምናልባት ኑሮ

(በውቀቱ ስዩም፥ የማለዳ ድባብ)

.

አይቦዝን አንቀልባው

አይሞላም ጉድጓዱ

ሺሆች ሞተው ቢያድሩ

ሺሆች ተወለዱ

ይመሻል ይነጋል

ያው እንደልማዱ፤

.

መሬት ባህር ሆኖ፥ድሀን ሰለቀጠው

ትልልቁ ቪላ፥ትንሹን ቤት ዋጠው

በመስታወት ጫካ፥በጡብ በብረት ደን

አየሁ ባደባባይ፥ሰው በሰው ሲታደን፤

.

ማን በገላገለኝ፥የጄን ሰዓት ሰብሮ

በምናልባት አገር፥በምናልባት ኑሮ

የመጣው ይምጣ እንጂ፥ማን ያቅዳል ደፍሮ።

.

77. ሀገርህ ናት በቃ

(ነብይ መኮንን ፥"ስውር ስፌት")

::

ይቺው ናት ኢትዮጵያ

ሀገርህ ናት በቃ!

በዚች ንፍቀ ክበብ፤

አይምሽ እንጅ መሸቶ፣ ማታው ከጠረቃ

የነቃም አይተኛ የተኛም አይንቃ።

ይቺው ናት ዓለምህ፤ ብቻዋን የተኛች

ከዓለም ተደብቃ!

አኪሯ ቀዝቅዞ፤ "ያንቀላፋች ውበት"

ያንተው የክት ዕቃ!

ምን ትሆን እንግዲህ ሀገርህ ናት እሷ!

ልቧን አታውልቃት አትጨቅጭቃት በቃ፤

አብረህ አንቀላፋ፤ ወይ አብረሃት ንቃ!!

ተጨማሪ ግጥሞችን በ

https://t.me/amharic_poem_gitm

ያገኛሉ።